# የአዲስ አበባ ስነ ምግባርና ፀረ- ሙስና ኮሚሽን

## የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር (የማሰልጠኛ ሞጁል)

## በኮሚሽኑ የተዘጋጀ




ሙስና ስጋት የማይሆንባት አዲስ አበባን እንፈጥራለን!

**ህዳር 2016 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**

ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**


አጠቃላይ የሞጁሉ መግቢያ ........ 0
የሞጁሉ አጠቃቀምና አቀራረብ ........ 2
የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ ........ 4
የሞጁሉ ይዘቶች ........ 4
ምዕራፍ አንድ ........ 5
የጥቅም ግጭት መሰረታዊ ሃሳቦች ........ 5
1.1 የጥቅም ግጭት ታሪካዊ ዳራ ........ 6
1.2 የጥቅም ግጭት ምንነት / Conflict of Interest / ........ 7
1.3. የጥቅም ግጭት አይነቶች ........ 8
1.4 የጥቅም ግጭት ገፅታዎች ........ 10
1.5. የጥቅም ግጭትና ሙስና ........ 10
1.6 የጥቅም ግጭትን መከላከል አስፈላጊነት ........ 12
1.7 የጥቅም ግጭት መንስኤዎች ........ 13
1.7.1. የጥቅም ግጭት መሰረታዊ መንስኤዎች ........ 13
1.7.2. የጥቅም ግጭት መኖርን የሚያሳዩ ሁኔታዎች ........ 15
1.8 የጥቅም ግጭት የሚፈፀሙባቸው መንገዶች ........ 17
1.9 ለጥቅም ግጭት ተጋላጭ የሆኑ የስራ ዘርፎችና አሰራሮች ........ 18
1.10 የጥቅም ግጭት የሚያስከትለው ጉዳት ........ 20
ምእራፍ ሁለት ........ 23
የጥቅም ግጭትን መከላከልና ማስተዳደር ስልቶች ........ 23
2.1. የውጭ ሃገራት ተሞክሮዎች ........ 25
2.2 በዓለም አቀፍ የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር ዘዴዎች ........ 27
2.3 በሃገራችን የተቀየሱ የጥቅም ግጭትን መከላከያ ስልቶች ........ 29
2.2.1 ሃገራዊ ህጎች ........ 30
2.3.2 ዓለም አቀፍና አሃጉራዊ ስምምነቶች ........ 31
2.4 የጥቅም ግጭትን በመከላከል በሃገራችን ተቋማት እየተወሰዱ ያሉ ተግባራት ........ 35
2.4.1 አሰራሮችና ማንዋሎች ........ 35

2.4.2 የመንግስት ሰራተኞች ስነ-ምግባር ደንብ ........ 36
2.4.3 የሙያ ስነምግባር ........ 37
2.5 የጥቅም ግጭት በመከላከልና በማስተዳደር መሰረታዊ ተግዳሮቶች ........ 38
2.6 በተቋማት ደረጃ ለሚፈፀም የጥቅም ግጭት ተግበራት መፍትሄ የሚሰጥባቸው መንገዶች ........ 40
ምዕራፍ ሶስት ........ 43
የጥቅም ግጭት የማስተዳደርና መከላከል የተለያዩ አካላት ሚና ........ 43
4.1 የጥቅም ግጭት የማስተዳደርና የመከላከል ኃላፊነት እና የተለያዩ አካላት ሚና ........ 44
4.1.1 ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው አካላት ........ 44
4.1.2 ሌሎች ባለድርሻ አካላት ........ 49

# አጠቃላይ የሞጁሉ መግቢያ

የአዲስ አበባ ከተማ የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 75/2014 ተቋቁሞ ሙስና መከላከልና ስነ ምግባር ግንባታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ ኮሚሽኑ ከተቋቋመ አንድ አመት ያህል ቢሆንም የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም መጠነ ሰፊ የግንዛቤ ግንባታና ማበልፀጊያ መድረኮችን እና ስልጠናዎችን ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል ሲሰጥ መቆየቱ ይታወሳል፡፡ ኮሚሽኑ መሰረታዊ፣ ወቅታዊ እና አንገብጋቢ በሚባሉ የሙስና እና ብልሹ ተግባራት መከላከል አሰራሮችና ስነ-ምግባር ነክ ርዕሶች ዙሪያ ማሰልጠኛና ግንዛቤ ማጎልበቻ የሚሆኑ ሞጁሎችን አዘጋጅቷል፡፡

በዚህ መርህ መሰረት በአሁኑ ወቅት ኮሚሽኑ እያዘጋጃቸው ከሚገኙ የስልጠና ርዕሶች መካከል ‹‹**የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር**›› የሚዳስስ ሰነድ ነው፡፡ ይህ የጥቅም ግጭት ዙሪያ የተዘጋጀ ሞጁል በቀዳሚነት የመንግስት የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች በጥቅም ግጭት ጉዳዮች ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ በማጎልበት፣ የጥቅም ግጭትን በመካላከሉ ረገድ የላቀ ኃላፊነት እንዲወጡ በሚስችል መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡

ይህንን ሞጁል /የስልጠና ሰነድ/ ለማዘጋጀት የኢፌዲሪ ህገመንግስት፣ የሙስና ወንጀልን የሚመለከቱ ህጎች፣ በሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲሁም በጥቅም ግጭት ላይ የተዘጋጁ የስልጠና ሰነዶች፣ አለምአቀፍና አህጉር አቀፍ ስምምነቶች፣ የአገር ውስጥ የምርምር ጽሁፎች፣ የፌደራል የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና ከባለሙያዎች ጋር የተደረጉ ውይይቶችና ሌሎችም በግብአትነት አገልግለዋል፡፡

የስልጠና ሰነዱ /ሞጁሎች/ ሶስት ክፍሎች ሲኖሩት የመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ የጥቅም ግጭት መሰረታዊ ጉዳዮችን የሚሸፍን ሆኖ ቀርቧል፡፡ በዚሁ ክፍል የሚሸፈኑት ፍሬ ሃሳቦች፤ የጥቅም ግጭት ምንነት፣ የጥቅም ግጭትን መከላከል አስፈላጊነት፣ የጥቅም ግጭት ከሙስና ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት፣ የጥቅም ግጭት ዓይነቶችና መፈፀሚያ መንገዶች፣ የጥቅም ግጭት የሚከሰቱባቸው ዋና ዋና የስራ አካባቢዎች፣ የጥቅም ግጭት የሚያደርሰው ጉዳት የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ምዕራፍ ሁለት የተለያዩ ሀገራትና እና ሃገራችን የጥቅም ግጭት ለመከላከያና ለማስተዳደሪያ የሚከተሏቸው ስርዓቶች፣ስልቶች፣ የተቀረፁ የህግ ድንጋጌዎች እንዲሁም የእነዚህ መከላከያ ስልቶች፣አንድነትና ልዩነት ይዳስሳል፡፡ የጥቅም ግጭትን በመከላከልና በማስተዳደር በምሳሌነት የሚጠቀሱ ሃገራት ተሞክሮዎች፣ ሃገራችን ነባራዊ ሁኔታዎች እንዲሁም የጥቅም ግጭትን በመከላከል ረገድ ተሞክሮዎች ይዳሰሳሉ፡፡

በመጨረሻ ምእራፍ ሶስት የጥቅም ግጭትን በመከላከል ረገድ የተለያዩ አካላት ሚና እና የእነዚሁ አካለት ኃላፊነት በዝርዝር ቀርቧል፡፡ በዚህም መሰረት የመንግስት፣ የፀረ-ሙስና ተቋማት፣ የመንግስት ተቋማት አመራርና ሰራተኞች፣ የሲቪክ ማህበራትና ሚዲያ ተቋማት ሚና እና ኃላፊነትን የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

ሰልጣኞች በሞጁሉ የተካተቱት ‹‹የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር›› ላይ የዳበረ ግንዛቤ እና ዕውቀት እንዲኖራቸው እንዲሁም እርስ በእርስ ተሞክሮ መለዋወጥ የሚያስችሉ የማነቃቂያ እና የቡድን ውይይት ጥያቄዎች ተካተዋል፡፡

በዚህ መሰረት ሰልጣኞች መልመጃ ጥያቄዎችንና ኬዞችን በግልም ሆነ በቡድን በመሥራትና በመወያየት ልምድና ግንዛቤቸውን የሚያዳብሩበት እድል ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

ሞጁሉ የ16 ሰዓት (ሁለት ቀን) ስልጠና ጊዜ የሚሸፈን ሆኖ የተዘጋጀ ነው፡፡

# የሞጁሉ አጠቃቀምና አቀራረብ

ይህ የማስልጠኛ ሞጁል ሲዘጋጅ ለአሰልጣኞችና ለሰልጣኞች የሚመች እና አሳታፊ በሆነ መንገድ ማቅረብ እንዲቻል የተዘጋጀ ነው፡፡ ለዚህም ሰልጣኞች ቀደም ሲል ካላቸው እውቀትና የስራ ተሞክሮ በመነሳት እየተወያዩና እየተከራከሩ ወደ ጋራ የመግባባት ደረጃ እንዲደርሱ የተለያዩ ተግባራት፣ መልመጃዎችና ኬዞች ቀርበዋል፡፡

ንዑስ ርዕሶች ለውይይት ከመቅረባቸው በፊት በግልና አጠገብ ለአጠገብ ያሉ ሰልጣኞች በሚቀርቡት ርዕሶች ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ይገልፃሉ፡፡ አሰልጣኙ በፅንሰ-ሃሳቦች ወይም በርዕሶች ዙሪያ በምሳሌ እና በተሞክሮ በተደገፈ ገለፃ እና ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ አሰልጣኙ የሚወያዩበት እንዲሁም በየርዕሶቹ መካከልና መጨረሻ የተቀመጡ የቡድን ወይይት ጉዳዮችና ጥያቄዎች ላይ በመነጋገር፣ በመከራከርና ሌሎች ማረጋገጫ ሃሳቦችን በማቅረብ ግንዜያባቸውና እውቀታቸውን የሚያዳብሩበትን ሁኔታ በሚፈጥር መንገድ የተዘጋጀ ነው፡፡

አሠልጣኙ ከሰልጠና ዓላማዎች፣ ርዕሶች ይዘቶች በመነሳት አጠር ያለና ሙያዊ ገለፃና ማብራሪያ በመስጠት ጠንካራ ድምዳሜ ላይ እንደሚደርስ ይታሰባል፡፡ በዚህ ሂደት በአብዛኛው አሰልጣኙ ስልጠናውን የማመቻቸት ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡

የሞጁሉ ይዘቶች፣ የመወያያ መልመጃዎችንና ተግባራትን ለማቅረብ የሚከተሉት ዋና ዋና ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡

**የቡድን ወይይት** (Group discussion)

የቡድን ውይይት ሰልጣኞች በተነሱ ጭብጦች ዙሪያ ካላቸው ቀደምት ልምድ ተነስተው ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ለማድረግ የምንጠቀምበት ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞችን በትንንሽ እና በትልልቅ ቡድን በማድረግ ማወያየትና ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ማድረግ ይገባል፡፡

**የአእምሮ ጓዳ ማንኳኳት** (Brainstorming sessions)

የአእምሮ ጓዳን ማንኳኳት ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ በተቀመጡ ጥያቄዎች መሰረት ቁልፍ ለሆኑ ሃሳቦች ሰልጣኞች ከቀደምት እውቀትና ልምዳቸው ተነስተው ሃሳባቸውን እንዲገልጹ የማነሳሳት ተግባር ነው፡፡

**ገለጻ** (Presentations)

ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ወይም ሃሳቦች ዙሪያ ሰልጣኞችን ለማገዝ በአሰልጣኞች አማካኝነት የሚሰጥ ገለፃ ወይም ማብራሪያ ነው፡፡

**ሚና ጨዋታ** (As a role play)

በትንንሽ ቡድን በመሆን ሰልጣኞች በቀረበው ኬዝ መሰረት የሚሰጣቸውን ሚና በመጫወት በተግባር የሚሆኑ ነገሮችን በድራማ መልክ ለማስገንዘብ እንዲረዳ ታስቦ የቀረበ ነው፡፡

**ኬዝ ጥናት** (Case studies) ፡

የኬዝ ጥናት በተግባር በተፈጸሙና እንደምሳሌ በቀረቡ ጉዳዮች ላይ ሰልጣኞች በቡድን፣ በጥንድ ሆነው እንዲወያዩ ታስቦ የቀረበ ስልት ነው፡፡

አሰልጣኞች እንደ ይዘቶቹ ሁኔታ፣እንደመለማመጃዎቹ ጠባይና እንደቀረበው ትእዛዝ ከላይ የቀረቡትን ስልቶች ተግባራዊ እንዲያደርጓቸው ይጠበቃል፡፡ይሁን አንጅ አሰልጣኞች በአማራጭነት ከቀረቡት የሥልጠና ተግባራት ወይም መልመጃዎች እና የአቀራረብ ሥልቶች ውጭ የተሻለ ዘዴ አለ ብለው ያመኑበትን ለመጠቀም ይችላሉ፡፡

## የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ

**ሰልጣኞች በዚህ ሞጁል የሰፈሩትን ጉዳዮች ከሸፈኑ እና ሰልጥናዉን ካጠናቀቁበ በኋላ፡-**

የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር አቅማቸውን በእውቀትና በአመለካከት በማሳደግ የተሰጣቸውን ሚናና ኃላፊነት በመረጃ ላይ በመመስረት በተቋማቸው ዉስጥ የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ለመከላከል ያግዛቸዋል፡፡

## የሞጁሉ ይዘቶች

**ምዕራፍ አንድ፡-** የጥቅም ግጭት መሰረታዊ ሃሳቦች

**ምእራፍ ሁለት፡-** የጥቅም ግጭትን መከላከልና ማስተዳደር ስልቶች

**ምእራፍ ሶስት፡-** የጥቅም ግጭት የማስተዳደርና መከላከል የተለያዩ አካላት ሚና

# ምዕራፍ አንድ

## የጥቅም ግጭት መሰረታዊ ሃሳቦች

*መግቢያ*

በአሁኑ ወቅት በመንግስት አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ስርዓት በዜጎች መብትና ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተሉ ከሚገኙት የሙስናና ብልሹ ተግባራት መካከል የጥቅም ግጭት አንዱ ነው፡፡ በዚህ የሞጁል ምዕራፍ በይበልጥ መንግስታዊ ተቋማት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ሰራተኞች እና የስራ ኃላፊዎች በጥቅም ግጭት ዙሪያ መሰረታዊ ግንዛቤ እንዲይዙ የሚያስችሉ ጉዳዮች ተካተዋል፡፡ ስለ ጥቅም ግጭት ታሪካዊ አመጣጥ፣ ምንነት፣ የጥቅም ግጭትን መከላከልና ማስተዳደር አስፈላጊነት፣ የጥቅም ግጭትና ሙስና አንድነትና ልዩነት፣ የጥቅም ግጭት መሰረታዊ መንስኤዎች፣ መገለጫ ባህሪያት፣ የጥቅም ግጭት የሚከሰቱባቸው ዋና ዋና የስራ አካባቢዎች፣ የጥቅም ግጨጭት የሚያስከትለው ጉዳት የሚመለከቱ ሃሳቦች በተናጠል እና በቡድን ከሚሰሩ የማነቃቂያ እና የቡድን ስራዎች ተደግፈው ቀርበዋል፡፡

**የምዕራፉ ዓላማ፡** - ሰልጣኞች ይህን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ፡-

የጥቅም ግጭትን፡-

- ታሪካዊ አመጣጥ እና ምንነት ላይ የዳበረ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፣
- ከሙስና ጋር ያላውን አንድነትና ልዩነት ያብራራሉ፤
- መከላከል አስፈላጊ መሆኑን ለሌሎች ያስረዳሉ፣
- መሰረታዊ መንስዔዎች እና ዓይነቶችን ያብራራሉ፣
- በመስሪያ ቤታቸውና በየተቋማቸው የጥቅም ግጭት አሰራሮችን ገፅታ ይገመግማሉ፣
- የሚያስከትሉትን ጉዳቶችን ይዘረዝራሉ፡፡

**የማሠልጠኛ ዘዴዎች**

- ገለጻ፤
- የጥንድና የቡድን ውይይት፣
- አስረጅ ጥናት፣
- ልምድ ልውውጥ፤

***የመርጃ መሣሪያዎች***

- ፓወር ፖይንት፤
- ማርከር፤
- ፍሊፕቻርት፣
- ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች (ስፖት፣ ድራማ)

**የምዕራፉ ርእሶች የሚሸፈኑበት** ጊዜ 7 ሰዓት

## 1.1 የጥቅም ግጭት ታሪካዊ ዳራ

***ማነቃቂያ ጥያቄዎች***

- የጥቅም ግጭት አስተሳሰብ መቼ ጀመረ ብላችሁ ታስባላችሁ?
- የጥቅም ግጭት በአብዛኛው ለምን ከመንግስትና ከህዝብ አስተዳደር ስርዓት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ሆኖ ይገለፃል?
- በሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ የጥቅም ግጭት ትኩረት የሚገባው ጉዳይ ነው ወይ? ለምን? እንዴት?

የጥቅም ግጭት ከመንግስት አስተዳደር ስርአት እድገትና መስፋፋት ጋር በተያያዘ እንደ አንድ የአስተዳደር አሰራር ጉድለት የተፈጠረ ክስተት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የጥቅም ግጭትም ተግባራት የመንግስት አስተዳደር ስርዓትና መዋቅር እያደገና እየተስፋፋ ሲሄድ ችግሩም እንደ ሌሎች እንደማንኛውም ብልሹ ተግባራት የመንግስት አሰራሮች ውስጥ ይንፀባረቅ እንደነበር የታሪክ ድርሳናትና ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡

የጥቅም ግጭት በመንግስትና በህዝብ አስተዳደር ስርዓት ውስጥ በባለስልጣናት የስራ ኃላፊነት እና የመወሰን ስልጣን የዕለት ከዕለት ተግባራት ሂደት ውስጥ የቆየ ታሪካዊ ገፅታ ያለው ቢሆንም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የተሰጠው ትኩረት እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም፡፡

ለዚህ ዝቅተኛ ግንዛቤ ቀዳሚ ምክንያት ከሆኑት ጉዳዮች መካከል፤ ለረጅም ጊዜ የነበሩ መንግስታዊ የአስተዳደር ስርዓቶች የሚዋቀሩትና የሚሰሩት የጥቂት ግለሰቦች ወይም በስልጣን ላይ ያሉ አካላትና ወገኖቻቸውን ፍላጎት፣ ጥቅምና ክብር ለማስጠበቅ በመሆናቸው ነው፡፡

የጥቅም ግጭት ተግባራት በመንግስት መዋቅርና አሰራር ውስጥ ስህተት፣ ጥፋትም አልፎ ተርፎም እንደ ወንጀልም መታየት የጀመረው ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ማለትም ‹‹ከኢንዱስትሪያል አብዮት›› መከሰት ወዲህ ስለ እኩልነት፣ የዜጎች መብት መከበር ተራማጅ

አስተሳሰቦች እና ፍልስፍናዎች በስፋት መቀንቀን ከጀመሩበት ግዜ ጀምሮ እንደሆነ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ሂደትም የመንግስት የአስተዳደር አሰራር፣ የባለስልጣናትና የስራ ኃላፊነትና ተግበራትና ሚና ምን መሆን እንደሚገባ በይበልጥ በአውሮፓ እና በሰሜን አሜሪካ ሃገራት ከቀድሞ ዘመን የተለዩ አስተሳሰቦች እየዳበረ እና እየተስፋፉ መሄድ ጀመረ፡፡

ካለፉት 50 እና 60 ዓመታት ወደዚህ በይበልጥ ከ‹‹ሚዲያ›› ቴክኖሎጂ እድገትና መስፋፋት ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እና መሰል ብልሹ ተግባራት የመንግስት አሰራርና ስርዓት የህዝብ ፍትሃዊ፣ ሚዛናዊ፣ የጋራ እና የዜጎችና የማህበረሰብን ሃብትና አጠቃላይ የመብት ጥቅም የማስከበር ጉዳይ ትኩረት እንዲያገኝ እና እንዲጠናከር ሆነ፡፡ ያም ሆኖ ሃገራት በጥቅም ግጭት ዙሪያ ያላቸው አቋም እና ለጥቅም ግጭት የሚሰጡት ትኩረት የሚወሰነው ከደረሱበት እና በሚገኙበት የአስተዳደር የእድገት ደረጃ እና በሚያራምዱት ርዕዮተ አለም ላይ ሆኖ ይወሰዳል፡፡

በአሁኑ ወቅት በይበልጥ ያደገና የዳበረ የዴሞክራሲ ስረዓት ላይ የደረሱ ሃገራት የመንግስት ባለስልጣንና ኃላፊነትን ለመያዝ ወይም ለመመደብ የግለሰቦች ብቃትና ስብዕና ከሚመዘኑባቸው መስፈርቶች አንዱ በጥቅም ግጭት ዙሪያ ያላቸው ግላዊ ታሪክ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም የጥቅም ግጭት ወደ ስልጣንና ኃላፊነት መመደቢያ መለኪያ ብቻ ሳይሆን፣ ከስልጣን መውረጃ ምክንያት አልፎ ተርፎም በወንጀል የሚያስጠይቅ የህግ ድንጋጌዎችም የተዘጋጁለት ጉዳይ ለመሆን በቅቷል፡፡

## 1.2 የጥቅም ግጭት ምንነት / Conflict of Interest /

***ማነቃቂያ ጥያቄዎች***

- የጥቅም ግጭት ሲባል ምን ማለት ነው?
- ለጥቅም ግጭት ትኩረት እየተሰጠ የመጣበትን ታሪካዊ እና ምክንያታዊ የለውጥ ሂደቶች ምን ይመስላችኋል? አብራሩ?

በአሁኑ ወቅት የጥቅም ግጭት ጽንሰ ሃሳብን በተለያዩ መንገዶች እና ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ በምሁራኖች እና የህግ መፃህፍት ግልፅ የሚባል ትርጉም ወይም ብያኔ ተሰጥቷቸው እናገኛለን፡፡ በአብዛኛው ስለጥቅም ግጭት ምንነት የተሰጡ ብያኔዎች ተቀራራቢና ተመሳሳይ በሚባል ደረጃ የተቀመጡና የቀረቡ ናቸው፡፡

በዚህ መሰረት የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ማለት አንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ወይም ኃላፊ በስራ ተግባር እና ኃላፊነቱ ዉስጥ ከህዝብ ወይም ከመንግስት፤ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግሉን፤የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመዱ የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም

ለማስቀደም ወይም ለማሳጣት የሚያችል ሁኔታዎች መኖር እንዲሁም ከመንግስታዊ ስራ ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጋጭ ወይም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ የሚያጋጥምበት ሁኔታ ነዉ፡፡

“የጥቅም ግጭት ማለት አንድ ሰው በአንድ ጉዳይ ላይ በዋነኛነት ሊያስከብረው የሚገባው የሕዝብ ጥቅም ወይም አደራ እና ከግል ጥቅም ጋር ሲጋጭ ወይም ግጭት ሊፈጥር የሚያስችል ሁኔታ ሲፈጠር ነው፡፡ (blacks law dictionary)

አብዛኛውን ጊዜ የጥቅም ግጭት የሚከሰተው የአንድ ሙያ ባለቤት ወይም የስራ ኃላፊ በጉዳዮች ላይ ዕለት ከዕለት በሚከውኗቸው ስራዎችና በሚወስኗቸው ውሳኔዎች ዙሪያ የተቋማትን ወይም የመንግስትና የህዝብን ጥቅምና መብት ወደጎን በመተው የግል ወይም የሌሎች አካላት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማስገኘት የሚያችሉ ግልጽ አጋጣሚዎች ወይም ሁኔታዎች ሲፈጥሩ ነው፡፡

ማንኛውም የስራ ኃላፊ ወይም ባለሙያ ሊያሳካው የሚገባ እና ከኃላፊነቱና ከሙያው የሚጠበቅ ተግባርና ኃላፊነት አለ፡፡ ሆኖም ግን የጥቅም ግጭት የሚከሰተው/ የሚስተዋለው ከዚህ ኃላፊነት በተዛባና ስርዓት በጣሰ መንገድ ውሳኔዎች ሲተላለፉ ወይም ስራዎች ሲሰሩ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ጠበቆች ህግን ሳይዛቡ የደንበኞቻቸውን ጥቅም የማስከበር ሃላፊነት አለባቸው፡፡ በተመሳሳይ ዳኞች ከአድሎአዊ በፀዳ መንገድ ፍትህን/ የዳኝነት ስራቸውን ማከናወን፣ ዓቃቤ ህግ የሕዝብና የመንግስትን ጥቅም ማስከበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆኖም የጥቅም ግጭት እነዚህ አካላት በኃላፊነታቸውና በሥራቸው ምክንያት ከተሰጣቸውና ከሚጠበቅባቸው የህዝብ ኃላፊነት እና የሙያ ሥነ-ምግባር በተቃራኒ ሁኔታ ለግላዊ ጥቅም ወይም የስጋ ወይም የጋብቻ ዘመዶቹ የሚያዘነብል ወይም የሚያስቀድም ሁኔታዎች፣ ባህሪያት እና ትክክለኛና ፍትሃዊ ስራዎችን እንዳይሰራ ያደርጋቸዋል ማለት ነዉ፡፡

## 1.3. የጥቅም ግጭት አይነቶች

***ማነቃቂያ ጥያቄ***

- የጥቅም ግጭት አይነቶች ናቸዉ ብላችሁ የምታዉቋቸዉ ካሉ ዘርዝሩና አብራሩ?

በአብዛኛው የጥቅም ግጭት ዓይነቶችን በሶስት ደረጃ ተከፍለው ይተነተናሉ፡፡

እነዚህም፡-

1. ተጨባጭ የጥቅም ግጭት (actual or real conflict of interest) ፣

2. **ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭት** (potential conflict of interest)

3. **መሰል የጥቅም ግጭት** (perceived conflict of interest) **የሚሉት ናቸው፡፡**

እነዚህ የጥቅም ግጭት ዓይነቶች ከዚህ በታች በተመለከተው መንገድ ለማብራራት/ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

**1.ተጨባጭ የጥቅም ግጭት /actual or real conflict of interest /**

ተጨባጭ የጥቅም ግጭት የሚፈጠረዉ የመንግስት ባለስልጣን ኃላፊነታቸውን በመወጣት ላይ በሚኖር ውጫዊ ተፅኖ ወይም የግል ፍላጎትም የመወሰን ኃላፊነቱን የሚፈታተን ሁኔታ ወይም ክስተት በተጨባጭ ወይም በትክክል ሲያጋጥም ነዉ ፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ የመንግስት ባለስልጣን ባለቤቱ ኮንትራክትር ብትሆን እና ባለስልጣኑ የሚመሩት ተቋም የሆነ ፕሮጀክት ለማሰራት ጨረታ ቢያወጣና የባለስልጣኑ ባለቤት ለመወዳደር የጨረታ ሰነድ ባለቤቷ በሚወሰነዉ መስሪያ ቤት ብታስገባ ባለስልጣኑ ተጨባጭ የሆነ የጥቅም ግጭት አጋጥሞታል ተብሎ ሊወሰድ ይችላል ፡፡

**2. ሊፈጠር የሚችል /ተጋላጭ የጥቅም ግጭት/potential conflict of interest**

ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭት በተጨባጭ ያላጋጠመ ነገር ግን አንድ የስራ ኃላፊ ወይም ባለሙያ ከሚሰራውና ከሚወስነው ውሳኔዎችና ተግባራት ጋር በተያያዘ የሚኖሩ አጋጣሚዎች ወይም ወደፊት ሊያጋጥም የሚችል እድልን የሚመላክት ሁኔታ ወይም ክስተት ነዉ፡፡

የሚከተሉት ምሳሌዎች ሀሳቡን ማጠናከሪያዎች ናቸዉ፡፡

ባለስልጣኑ የተሰጠዉን ሃላፊነት እየተወጣ ሳለ ባለቤቱ ኮንትራክተር ለመሆን ንግድ ፍቃድ ካወጣች አሁን በተጨባጭ ያልተፈጠረ ነገር ግን ወደፊት የመከሰት ሁኔታዉ ሰፊ ነዉ ፡፡

አንድ የሰዉ ሀብት ዳሬክተር ልጁ ዩንቨርሲቲ እየተማረ ያለ፣ አሁን በተጨባጭ ያጋጠመዉ ሁኔታ የሌለ ፣ ነገር ግን ወደፊት ትምሀርቱን አጠናቆ ስራ መፈለግ ሲጀምር እና አባቱ ያለበት ተቋም የስራ ቅጥር ቢያወጣ የጥቅም ግጭት የመከሰት እድሉ ሰፊ ነዉ፡፡

### 3. መሰል/ግምታዊ የጥቅም ግጭት /perceived conflict of interest /

መሰል ወይም ግምታዊ የጥቅም ግጭት ሶስተኛ ወገን ወይም ህዝብ የመንግስት አካል አሁን በተጨባጭ ወይም ወደፊት የመወሰን ተፅዕኖ ያደርሳል ተብሎ ሲገምት ወይም መስሎ ሲታይ ነዉ፡፡ የሚከተሉት ምሳሌዎች ሀሳቡን ማጠናከሪያዎች ናቸዉ፡፡

የአንድ ተቋም የሰዉ ሀብት ዳይሬክተር ልጁ ከዩንቨርሲቲ ተመርቆ እንደመጣ በተቋሙ ቢቀጠር ዳይሬክተሩ ለራሱ ልጅ እንደሚያዳላ እና የመወሰን ስልጣኑ ላይ ተፅኖ እንደሚያሳርፍ ግምት ሲወሰድ ወይም መስሎ ሲታይ ነው፡፡

## 1.4 የጥቅም ግጭት ገፅታዎች

የጥቅም ግጭት ገፅታ በሚከተለው መንገድ ተለይቶ ሊገለፅ ይችላል፡፡

1. **ገንዘብ ነክ የሆነ**

በገንዘብ ነክ የሆነ ፍላጎት አንድ የመንግስት ሰራተኛ ወይም ኃላፊ በተሰጠዉ ኃላፊነት አጋጣሚዎችን በመጠቀም ማንኛዉንም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኙ ጥሬ ገንዘብን ጨምሮ፣ ስጦታዎች፣ ቅናሽ ወይም ነፃ የተለያዩ አይነት ግብዣዎች፣ አገልግሎቶችን ለራስ ወይም ለቤተሰብና ለቅርብ ዘመድ ማግኘት/ማስገኘት ወይም ማሳጣትን የሚያካትት ነዉ ፡፡

2. **በገንዘብ ነክ ያልሆኑ**

ገንዘብ ነክ ያልሆነ ፍላጎት ወይም ጥቅም ማግኘት ሲባል፣ የመንግስት ባለስልጣን እና ሰራተኛ ለራስ፣ ለቤተሰብ፣ ለጓደኛ፣ ለራስ የኃይማኖት ተቋም ፣ ስፖርት ቡድን፣ ለራስ ባህል …ወዘተ፣ በመወገን ወይም በማድላት ውሳኔዎችን በማዛባት ጥቅሞችን ለማስገኘት በሚደረግ እንቅስቃሴ ዉስጥ የሚፈጠር የፍላጎት ዓይነት ነው፡፡

## 1.5. የጥቅም ግጭትና ሙስና

**ማነቃቂያ ጥያቄ**

- የጥቅም ግጭትና ሙስና የሚመሳሰሉባቸውና የሚለያዩባቸው ባህሪ አላቸው ብለው ያምናሉ? ለምን? እንዴት ? ምክንያታችሁን አቅርቡ?

ከጥቅም ግጭት ባህሪ የተነሳ (ገቢ ያልሆነ ጥቅም የማግኘትና የማስገኘት) በሌላ በኩልም በዚህ ድርጊት ሌሎች አካላት ላይ በሚያደርሰው ጉዳት የተነሳ የጥቅም ግጭት ከሙስና ተግባር ጋር

አንድና ተመሳሳይ ባህሪያት አላቸው። በዚህ ምክንያት ሙስና እና የጥቅም ግጭት ተዛማጅነትና ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ሆነው ይወሰዳሉ።

ሌላው ሁለቱንም ሃሳቦች አንድና ተመሳሳይ የሚያደርጋቸው ዋናው ጉዳይ ሁለቱም የተሰጠን ስልጣንና ኃላፊነትን ለግልና ለሌሎች መጠቀሚያ የማድረጊያ እድልና አጋጣሚ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው ነው።

በአጭር አገላለፅ የጥቅም ግጭት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነትና ስልጣን ባለበት ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ እንደሚኖር ይታመናል፣ ስለዚህ የጥቅም ግጭት በመኖሩ ብቻ የሙስና ወንጀል/ ተግባር ተፈፀሚል ወደሚል ድምዳሜ መደረስ የለበትም። በዚህም የጥቅም ግጭት ከሙስና ፅንሰ ሃሳብ የጠበበና በተወሰኑ ጉዳዮችና ድርጊቶች ዙሪያ ላይ ብቻ የሚያተኩር ሆኖ ይወሰዳል።

በሌላ አገላልፅ ለምሳሌ አንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ቤተሰቡ ወይም የቅርብ ዘመዱ የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም ከስራውና ከኃላፊነቱ ጋር በቀጥታ ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታዎችን መኖሩ፣ ማወቁና በእነዚህ አጋጣሚዎች ውስጥ መስራቱ ሙስና ተፈፀመ ወይም ለመፈፀም ተዘጋጅቷል ሊስብለው አይቻልም።

ምንም እንኳ የጥቅም ግጭት ሙስና እንዲፈጸም ምቹ አጋጣሚዎችን ወይም መደላድልን የመፍጠር እድል ቢኖረውም፣ የጥቅም ግጭት ባለበት ሁኔታዎች ወይም አጋጣሚዎች ውስጥ ሁሉ ግን የሙስና ተግባር ላይኖር ይችላል። ነገር ግን ሙስና በተፈፀመበት/ በተከሰተበት ሁኔታ ውስጥ የጥቅም ግጭት የመከሰት እድል እንዳለው መገንዘብ ተገቢ ይሆል።

## የቡድን ውይይት

የአንድ ድርጅት የስራ ኃላፊ መ/ቤታቸው ሊገዛቸው የፈለጋቸው ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ንብረቶችን፣ የመስሪያ ቤቱ ባልደረባ ከሆኑ ግለሰብ የንግድ ድርጅት እንዲገዛ በኮሚቴ ያስወስናሉ። ለዚህ ውሳኔ መሰረታዊ ምክንያቶች ሆነው የቀረቡትና በኮሚቴ የታመነባቸው ሃሳቦች መካከል አንዱ የሚገዙት ዕቃዎች ከሌሎች አቅራቢዎች ያነሰ ዋጋ ያላቸው መሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአቅራቢው ደርጅት ባለቤት ወይም የስራ ባልደረባቸው ለረጅም ጊዜ ያሰቃየው የነበረውን ህመም ወይም የጤና ችግር በውጪ ሃገር ህክምና እንዲያገኝ የሚስችላቸው መሆኑ ጭምር ነው። በኮሚቴው በተደረሰው ስምምነት መሰረት ከፍተኛ መጠን ያለው ንብረት ግዥ ተፈፀመ። ለዚህም ምስጋና የሚሆን የአቅራቢው ቤተሰቦች ለኮሚቴው ከፍተኛ የሆነ ግብዣ እና ለስራ ኃላፊውም የማስታወሻ ስጦታ ስነ ስርዓት ተካሄደ።

- **ከላይ በቀረበዉ የመወያያ ሀሳብ ተነስታችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩ፡፡**
  1. በዚህ ሂደት ውስጥ የተስተዋሉ ተግባራትን ከጥቅም ግጭትና ከሙስና ተግባራት ጋር በማነፃፀር ሁለቱ ፅንሰ ሃሳቦች ያላቸውን ተዛምዶና ትስስር አስረዱ/ አብራሩ?
  2. ከዚህ ሂደት (ከሙስና እና ጥቅም ግጭት ) ተግባራት መካከል ከፍተኛ ጉዳት ያለው/ የሚያስከትለው ተግባር የትኛው ነው? ለምን?

## 1.6 የጥቅም ግጭትን መከላከል አስፈላጊነት

***ማነቃቂያ ጥያቄዎች***

- **ከታች የተቀመጠዉን ጥያቄዎች አጠገባችሁ ካሉ ሌሎች ተሳታፊዎች ጋር በመነጋገር ማብራሪያ ስጡ፡፡**
  1. የጥቅም ግጭት ለምን የትኩረት አቅጣጫ እየሆነ መጣ?
  2. የጥቅም ግጭትን መከላከል አስፈላጊነትን አስረዱ?

በዘመናዊ የመንግስት አስተዳደር ስርዓት ለስራ ውጤታማነት እና ምርታማነት ከፍተኛ ችግር እየሆነ የመጣው የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከሰት ምክንያየት የሚሆነዉ የጥቅም ግጭት እንደሆነ ሙስናና ብልሹ ተግባራትን በመከላከል ላይ የተሰማሩ አካላት ያስገነዝባሉ፡፡ በሀገራት ደረጃም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ ህጎች እና የሙስና መታገያ ስልቶች የመንግስት ስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በጥቅም ግጭት ተግባራት ውስጥ እንዳይገቡ የተለያዩ መከላከያ ስርዓቶች መዘርጋትና መተግበር አስፈላጊነት ተቀባይነትና ስምምነት ያገኘ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል፡፡

ይህም የሆነበት ቀዳሚ እና መሰረታዊ ምክንያት የጥቅም ግጭት መከላከል በሃገር ሁለንተናዊ እድገት፣ ልማት፣ ፀጥታ እና መልካም አስተዳደር እንዲሁም በዜጎች መብት መከበር ላይ ያለው አወንታዊ የላቀና የጎላ በመሆኑ ነው፡፡

በጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት አስፈላጊነትን ከሚያመለክቱ በርካታ መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል የሚከተሉትን በምሳሌነት ተዘርዝረዋል፡፡

የመንግስት አስተዳደር እና ተቋማት አሰራር ፍትሃዊ እንዲሆን ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዳ፣ አገልግሎት አሰጣጦች ፍትሃዊና ሚዛናዊ እንዲሆኑ ፣ የዜጎች መብትና ጥቅም እንዲከበር በማድረግ ዜጎች በመንግስት ላይ ያላቸው አመኔታ እንዲጎለብት ያደርጋል፡፡

በመንግስት አሰራርና ሃብት አጠቃቀም፣ ውሳኔ አሰጣጥ ዙሪያ የግልፅነት እና የተጠያቂነት አሰራሮችን በማሻሻል የመልካም አስተዳደር ስርዓትን ያሳድጋል፡፡

የመንግስት ስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የሚሰሯቸውና የሚወስኗቸው የህዝብና የሃገርን ጥቅምና መብት ያከበረ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል፤

የመንግስት ሃብትና ንብረትን ህግና ስርዓትን በተከተለና ውጤታማ በሆነ መንገድ በመጠቀም የሃገር እድገትና ልማት ማሳደግ ላይ ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ እድሆን ያግዛል፡፡

ነፃ የገበያ ( ጨረታ፣ ግዢ፣ ቅጥር ወዘተ ) አሰራሮችን ግልፅና ፍትሃዊ ስርዓትን እንዲከተሉና ዜጎች በይበልጥም የግብር ከፋዩን መብትና ጥቅም ለማስከበር ይረዳል፣

የመንግስት አሰራርን ቀልጣፋ በማድረግ፣ ኢንቨስትመንትን በማሳለጥ፣ ፍትሃዊ አሰራርን በማስፈን፣ የዜጎችን የእኩልነት መብት ያጎለብታል፡፡

## 1.7 የጥቅም ግጭት መንስኤዎች

***ማነቃቂያ ጥያቄ***

የስራ ክፍላችሁን ወይም የተቋማችሁን አሰራሮች ምሳሌ በመውሰድ የጥቅም ግጭት የሚከሰትባቸውን መሰረታዊ መንስኤዎች የምትሏቸውን ጉዳዮች ዘርዝሩ?

### 1.7.1. የጥቅም ግጭት መሰረታዊ መንስኤዎች

የጥቅም ግጭት እንደ አንድ የሙስና ወንጀል ዓይነት መሰረታዊ መነሻ ምክንያት የባህሪ ወይም የስነ-ምግባር መጓደል ሲሆን፣ በዚህ በተለያዩ ኃላፊነት ቦታ ላይ የተቀመጡ አካላት ኃላፊነትና ሙያቸውን ለተቋማቸውና ለተመደቡበት ቦታ ሳይሆን ለራሳቸው ወይም ለሌሎች አካላት ጠቀሚያ የማድረግ ውሳኔ ሲወስኑ ወይም ስራ ሲሰሩ፣ ደካማ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ሲኖር የሚፈጠር ችግር ነው፡፡፡

እነዚህ ፍሬ ሃሳቦች በሚከተለው ሁኔታ ተብራርተዋል፡፡

ሰዎች የተጣለባቸውን እምነትና ኃላፊነት ወደ ጎን በመተው ከሙያና ህጋዊ አሰራር ባፈነገጠ ሁኔታ ለራሳቸውና ለሌሎች ተገቢ ያልሆነ ጥቅም እንዲያገኙ ሲሉ ውሳኔዎችን የማዛባት፣ የግል ተገቢ ባልሆነ መንገድ ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ለማስከበርና ለማግኘት ተገቢ ያልሆኑ ሁኔታዎች የመፍጠር እና የማመቻቸት ስራ ሲያከናውኑ ነው፡፡

የአሰራር ስርዓት ክፍተቶች እና እነዚህ ክፍተቶችን ለማረም ጥረት አለማድረግ፣ ደካማ የቁጥጥር የክትትልና የተጠያቂነት አሰራር እና ደካማ የመልካም አስተዳደር ስርዓት፣ ለደባል ሱስ ተጋላጭ መሆን ሌሎች ለጥቅም ግጭት የሚዳርጉ የስነ-ምግባር ድክመቶች ናቸው፡፡

በተጨማሪም የዲሞክራሲ ስርዓት ባልዳበረባቸው እና በድህነት ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሀገሮች የመንግስት ባለስልጣናትና ባለሙያዎች የጥቅም ግጭት የመፈፀማቸው ሁኔታና ደረጃ ከፍተኛ ነው፡ ፡

ከእነዚህ መሰረታዊ ምክንያቶች በተጨማሪ የሚከተሉትም ሃሳቦች ለጥቅም ግጭት መከሰት ምክያቶች የሚሆኑ ናቸው፡፡

ከፍተኛ የሆነ ግላዊ ገንዘብ ነክ እና ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ጥቅሞች ( ስሜትን ለማስደሰት፣ በሌሎች ዘንድ የግል ዝናና ክብር፣ ወዘተ..) ተቀባይነት ለማግኘት፣

በተለያዩ ግላዊና ቡድናዊ ፍላጎትን መሰረት ባደረገ የግለሰብና የመንግስትን መብት እና ጥቅም ለመጉዳት የሚደረግ እኩይ ተግባራት ሌሎች ተጨማሪ የጥቅም ግጭት ሳቢ ምክንያቶች ሆነው ይገለፃሉ፡፡

## የቡድን መወያያ ጥያቄ

በአንድ ወቅት በስራ ኃላፊነት የምትመራው ተቋም ባወጣው የግንባታ ስራ ጨረታ ለረጅም ጊዜ ስትመኘው የነበረ ባለሙያ ድርጅት የውድድር ሰነድ ማስገባቱን አወቀች፡፡ የስራ ኃላፊዋና እና ባለሙያው በቦርድ አመራርነትና አባልነት በመስራት ቆየት ያለ ትውውቅ አላቸው፡፡ በመጨረሻም የስራ ኃላፊዋ የባለሙያው ድርጅት የጨረታው አሸናፊ መሆኑን በስልክ አሳወቀችው፡፡ እሱም በማሸነፉ አመስግኖ፣ ለቀጣይ ውይይት እና የሻይ ግብዣ ቀጠሮ ያዙ፡፡ በእለቱም የስራ ኃላፊዋ ላደረገችው ውለታ የስምት መቶ ሺ ብር ቼክ በስጦታ መልክ ቢያቀርብም የስራ ኃላፊነቷና ስነምገባሯ የማይፈቅድላት መሆኑን ነገረችው፡፡ ይልቅኑ ገንዘቡን በግል ላቋቋመችው የበጎ አድራጎት ድርጅት እንዲለግስ አድራሻ ሰጠችው፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚስተዋል የጥቅም ግጭት እና የሙስና አዝማሚያዎች አሉ ወይ? በምን መንገድ ይገለፃል?

## 1.7.2. የጥቅም ግጭት መኖርን የሚያሳዩ ሁኔታዎች

***ማነቃቂያ ጥያቄ***

*የጥቅም ግጭት ተከስቷል ወይም ሊከሰት ነው ብለው የሚመላክቱ ወይም የሚጠራጥሩ መገለጫዎችን፣አመላካች ሁኔታዎችና የጥቅም ግጭት መፈፀሚያ መንገዶችን ዘርዝሩ?*

እንደሚታወቀው የጥቅም ግጭት ተግባር አፈፃፀም ሂደት ስውር እና በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈጸም ተግባር ነው፡፡ በዚህ ባህሪው የተነሳ በግልፅና በቀጥታ የሚፈጸም ባለመሆኑ፣ ተጨባጭ ማስረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡

ሆኖም በአንድ የስራ አካባቢ ወይም የስራ ዘርፍ የጥቅም ግጭት መፈፀሙን እና የፈፃሚዎቹን ማንነት የሚጠቁሙና የሚያመላክቱ ሁኔታዎች እንደ ሰዎች ግንዛቤና የዕውቀት ደረጃ ሊወሰን ይችላል፡፡ ከእነዚህ የግምት መስፈርቶች መካከል ከተለመደው የተለዩ ያልተለመዱ የግለሰቦች የግል ህይወት ለውጥ፣ ግላዊ ግንኙነቶ እና የስራ አካባቢ እንቅስቃሴ ጥቅም ግጭት መፈፀሙን ሊጠቁሙና ሊያመለክቱ የሚችሉ ቀዳሚ ምልክቶች ናቸው፡፡

ከእነዚህ ጠቅላላ ሃሳቦች በተጨማሪ በተለያዩ ፅሁፎች የሚገለፁ የጥቅም ግጭት መፈፀሙን አመላካች ከሆኑ ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

- ከመንግስት እና ከሕዝብ ጥቅም ጋር የሚጋጭ የግል ገንዘብ፣ ከመሠረታዊ ፍጆታ እና አቅም በላይ የሆነ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ማፍራት ሲኖር፣
- ከመንግስት ሀላፊነቱ ጋር በሚጋጭ መንገድ በሽርክና፣ በግል ባለሃብት ፣ በአማካሪነት፣ በቦርድ አመራርነት፣ በዳይሬክተርነት እና በአክሲዮን ባለድርሻነት ተሳትፊዉ ሲገኝ፣
- የትርፍ ተካፋይ እና ሌሎች ለጥቅም ግጭት በሚዳርጉ ስራዎች ላይ ሲሰማራ፣
- በመንግስት ሀላፊነቱ ግዥና ሽያጭ ሲፈፅም፣ የሥራ ፈቃድ እና እድሳት ሲሰጥ፣ ግብር እና ታክስ ሲተመንና ሲያረጋግጥ፣ ውል ሲሰጥ እና ሌሎች ለጥቅም ግጭት በሚዳርጉ ስራዎች ላይ ሲሰማራ፣
- በትዳር ጓደኛ፣ በልጆች፣ በቅርብ ዘመዶች እና በንግድ ሸሪኮች አማካኝነት ከመንግሥታዊ ኃላፊነቱ ጋር የሚጋጭ ጥቅም ሲያገኝ፣
- በኃላፊነት በሚሠራቸው ሥራዎች አማካኝነት ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም ተመሳሳይ ጥቅሞችን የሚያገኝ ሲሆን ነው፡፡

- ስጦታዎችን፣የጉዞ ፣መስተንግዶ ግብዣዎችን እና ማንኛዉም ኢኮኖሚያዊ ዋጋ ያላቸዉን ቁሶች እና አገልግሎቶችን ለራስ እና ለቤተሰብ መቀበልና መጠቀም፣
- የመንግስት ባለስልጣን ከድርጅቶች በግል ህይወቱ እዳ እና ዉለታ ካለበት፣
- የመንግስትን እና የህዝብን ንብረትና ገንዘብ ለግል እና ለቤተሰብ ጥቅም ማዋል፡፡ ለምሳሌ፡- የመንግስትን የስራ ሰዓት ለሌላ ተግባር ማዋል ፣የመንግስትን ተሽከርካሪ፣ የቢሮ ስልክን፣ የፅህፈት መሳሪያዎችን …ወዘተ ለግል ጥቅም ማዋል፣
- ከመንግሥታዊ ኃላፊነት በተጨማሪ በካምፖኒ አማካሪነት፣በዳይሬክተርነት፣ በሕዝባዊ ማህበራት፣ በአክሲዮን ባለድርሻነት መሥራት፣
- ሚስጥራዊ መረጃዎችን ወይም በስራ ምክንያት ያወቁትን ድብቅ መረጃዎች ለግል ጥቅም የማዋል ተግባር፤
- መንግሥታዊ ኃላፊነት ከግል ጥቅም ጋር መጋጨቱን እያወቀ አስፈላጊውን እርምጃ ከመውሰድ መቆጠብ፣
- ኃላፊነቱን ከለቀቀ በኂላ ቀድሞ ይሠራበት በነበረ መሥሪያ ቤት ውስጥ ከ2 ዓመት በፊት በአማካሪነት፣ ውል በማዘጋጀትና በማዋዋል፣ በመሥሪያ ቤቱ በሚያወጣው ጨረታ መሳተፍ፣ ከኃላፊነቱ ጋር የተዛመደ ጥቅም የሚያስገኝ ሥራን መሥራት ፡፡

## የቡድን መወያያ ጥያቄ

አንድ በቅንነቱ የሚታወቅ ከፍተኛ ሙያ እና ልምድ ያለው የአንድ ድርጅት ባለሙያ፣ በቅርብ ጊዜ ለሚሰራበት ድርጅቱ ያገኘውን አዲስ የፈጠራ ስራ ዕውቅና እንዲሰጠው ለአንድ የውጪ ሃገር ኩባንያ ላከው፡፡ በዚህም የተነሳ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለፈጠራ ስራው እውቅና እና ሽልማት ተሰጠው፡ ፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚሰራበት ድርጅት የተሸለምከውን ሽልማትም ሆነ ዕውቅና ለድርጅቱ ማስረከብ አለብህ፣ አለበለዚያ የጥቅም ግጭት ስለፈፀምክ ለዲስፕሊን ትቀርባለህ የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጠው፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኂላም ጉዳዩን ቀድሞ የድርጅቱ ነገረ ፈጅ የነበረውና በአሁኑ ወቅት በፕሬዝዳንትነት ወደሚመራው ፍ/ቤት ለማቅረብ ከዳኛው (ፕርዝዳንት) ጋር እየተነጋገር ይገኛል፡፡

- በዚህ ሂደት ውስጥ የጥቅም ግጭት ገፅታዎችን እንዴት ትረዱታላችሁ? በጉዳዩ ላይ በዝረዝር ተነጋገሩበት

## 1.8 የጥቅም ግጭት የሚፈፀሙባቸው መንገዶች

የጥቅም ግጭት በተለያዩ ሁኔታዎችና መንገዶች የሚስተዋሉና የሚያጋጥሙ ቢሆንም፣ ድርጊቶቹን በመፈፀም ሂደትና የጥቅም ግጭቶች ዓይነት ተመሳሳይነት ባላቸው ስልቶች አማካኝነት ይፈፀማሉ።

ከእነዚህ የተለመዱ መንገዶች መካከል የሚከተሉት ቀዳሚ ተጠቃሽ ናቸው።

**ለራስ ፍላጎትና ጥቅም ማመቻቸት / Self-dealing / ፦** በአንድ ድርጅት ከፍተኛ ሙያና የመወሰን ስልጣን ያለው የስራ ኃላፊ የሚሰራበትን ተቋም ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም ውለታ፣ ስራዎች) ወደ ራሱ ( ላቋቋመው ድርጅት) አሳልፎ መስጠት ወይም የማመቻቸት ኢ-ስነምግባራዊ ስራዎችን መስራት ነው። ይህ የአሰራር ሁኔታ የብዙ አይነት የጥቅም ግጭት መፈፀሚ መንገድ ነው።

**ስጦታ / Gift /፦** ይህ ተግባር / ድርጊት በይበልጥ በአደጉ ሃገሮች በከፍተኛ ደረጃ የሚስተዋል የጥቅም ግጭት ዓይነት ነው። የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ከእነሱ ከሚሰሩበት ተቋም ጋር ተመሳሳይነት ወይም ተቀራራቢነት ያለው ስራ ከሚሰሩ አካላት የተለያዩ ስጦታዎችን፣ በጉርሻ መልክ፣ በመስተግዶ፣ የውጪ ሃገር ጉብኝት፣ በመድህና እና የህክምና ክፍያ ሽፋን፣ ወዘተ ውሳኔና ስራዎችን የማዛባት ከፍተኛ አቅም ያላቸው ተግባራት ናቸው።

**ሚስጢራዊ መረጃዎችን ለግል ጥቅም አሳልፎ መጠቀም / insider trading / ፦** የጥቅም ግጭት ከአንድ ወገን ጥያቄና ፍላጎት የሚነሳ ሳይሆን ከሁለት የተለያዩ አካላት ሊመነጭ የሚችል ተግባር ጭምር ነው። ለዚህ አባባል አንድ መገለጫ የተቋማትን ጥብቅ ሚስጢሮችን የሚያውቅና የማወቅ እድሉና ስልጣኑ ያለው የስራ ኃላፊና ባለሙያ ሚስጢሮችን ለሌሎች አሳልፎ በመስጠት የግሉን ጥቅምና ፍላጎት ማሳኪያ መደራደሪያ መሳሪያ ሊደረግ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ሲከሰቱ ይስተዋላል። ለምሳሌ፦ አንዳንድ ግዢ ፈፃሚ ተቋማት አቅራቢ ድርጅቶችን በግል በመደራደርና ሚስጢራዊ መረጃዎችን አሳልፎ በመስጠት በግላቸው ተጠቃሚ ለመሆን የጥቅም ግጭት ተግባራትን ሊጀምሩ/ ይችላሉ።

**ዝምድና / Nepotism / ፦** ሰዎችን ከህጋዊና ፍትሃዊ አሰራር ባፈነገጠና መድሎን እና ሚዛናዊ አሰራርን ባልተከተለ መንገድ የቅርብ ዘመድን፣ ጓደኛን ወይም በሌላ መንገድ ያለ ግንኙነትን መሰረት በማድረግ ቅጥር መፈፀም ወይም ማመቻቸት፣ የውስጥ ስራ ደረጃ እድገት፣ በስራ ቦታዎች ላይ ከሌሎች በተለየ በተዛባ መንገድ ተገቢ ያልሆነ ድጋፍ እና ልዩ ጥቅም እንዲያገኙ ማድረግ አንዱ የጥቅም ግጭት መፈፀሙን አመላካች አሰራር ነው።

የጥቅም ግጭት የሚከሰቱባቸው ሌሎች ተግባራት፡-

**የውጪ ስራ** /outside employment/ **በመስራት** ፡- (አንድ መንግስት ግብር መዳቢ ሰራተኛ የአንድ ነጋዴ ሂሳብ የሚሰራ ቢሆን ግጭት ይፈጥራል) ፣

**የገዘብ ጥቅም** /financial interest/ ፡- አንድ የጨረታ ኮሚቴ አባል የሆነ ሰራተኛ በጨረታ ከሚሳተፉ ተወዳዳሪ ድርጅቶች ውስጥ በአንዱ ባለ አክሲዮን ቢሆን ባለአክሲዮን የሆነበት ድርጅት እንዲያሸነፍ ጥረት ሊያደርግ ይችላል፡፡

**በዘመድ መስራት፡-** የመንግስት ሰራተኞች የህዝብ አገልጋዮች ፣ በዘመድ በጋብቻ፣ በጓደኛነት፣ ወዘተ… በመስራት በሚያገለግሉት ህዝብ መካከል ልዩነት በመፍጠር የሚከሰቱ ናቸው፡፡

**የቡድን መወያያ ጥያቄ**

በአንድ ተቋም የስራ የውስጥ እድገትና የትምህርት እድል የሴቶች መብት መጠበቅ በሚል የማኔጅመንት ውሳኔ ብዛት ያላቸው የተቋሙ ሴት ሰራተኞች በአጭር ጊዜ ውስጥ የእድሉ ተጠቃሚ በመሆን የተቋሙ ከፍተኛ የስራ ኃላፊነትን ለመቆጣጠር ቻሉ፡፡ በዚህ ሂደት ትምህርትና እድገት ካገኙት ሴት ባለሙያዎች መካከል ሶስት የስራ ኃላፊዎች የትዳር ጓደኛ ለመሆን በቁ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተቋሙ አሰራር ቅሬታ መታየት ጀመረ፡፡ በዚህ ሂደት የሚስተዋል የጥቅም ግጭት ምን መልክ አለው? አብራሩ፡፡

## 1.9 ለጥቅም ግጭት ተጋላጭ የሆኑ የስራ ዘርፎችና አሰራሮች

**ማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- ከታች የተቀመጡትን ጥያቄዎች በቡድን ወይም አጠገባችሁ ካሉ ሌሎች ተሳታፊዎች ጋር በመነጋገር ማብራሪያ ስጡ፡፡

1. የጥቅም ግጭት የማይፈፀምባቸው የስራ አካባቢዎች እና አሰራሮች የሉም ብለው ያምናሉ? ለምን? በምሳሌ አስረዱ?
2. የተቋማትን የጥቅም ግጭት ተጋላጭነት ደረጃ የሚወስኑ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? አብራሯቸው?
3. የስራ ክፍላችሁን ወይም የተቋማችሁን አሰራሮች ደረጃ ለጥቅም ግጭት መከሰት መሰረታዊ ምክንያቶች የምትሏቸውን ጉዳዮች ዘርዝሩ?

የጥቅም ግጭት በማንኛውም የመንግስት አሰራርና ውሳኔ አሰጣጥ ሁኔታዎች ውስጥ የሚኖሩና የሚፈጠሩ ቢሆኑም በሁሉም የስራ አካባቢዎች እና ዘርፎች በተመሳሳይ ደረጃ፣ ዓይነት እና መጠን ይስተዋላሉ ማለት ግን አይደለም፡፡ በስራ ባህሪያቸው አንዳንድ አሰራሮች እና የስራ ዘርፎች ለጥቅም ግጭት መከሰት/ መፈፀም ከሌሎች በበለጠ ተጋላጭ ናቸው፡፡

ለአብነት ያህል ከገቢና ጉምሩክ፣ ግብር ሰብሳቢ ሴክተሮች፣ ኢንቨስትመት፣ ንግድ ፍቃድ ሰጪ ተቋማት፣ መሬት አስተዳደር፣ የፍትህ ስርዓት፣ ኮንስትራክሽን፣ የሰራተኛ ቅጥር እና ግዢ ወዘተ ስራ ጋር በተያያዘ የሚሰሩ አካላት እና የስራ ክፍሎች ለጥቅም ግጭት አሰራር የበለጠ ተጋላጭ ናቸው፡፡ በስራ ሂደት ደረጃ በጨረታ፣ ግዥ፣ ቅጥር፣( የአገልግሎት፣ የአማካሪ፣ ዕቃዎች…)፣ ቁጥጥርና ክትትል ፍቃድ የመስጠት ስራዎች፣ ቀዳሚ ተጋላጭ የጥቅም ግጭት ተጋላጭ የሆኑ ናቸው፡፡

የጥቅም ግጭት የሚፈጸምባቸው ሁኔታዎች እና አመላካች ምሳሌዎች

የመንግስት መ/ቤቶች በሚያወጡት ጨረታ ላይ ለመሳተፍ ከሚፈልጉ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያላቸዉ የሚመለከታቸዉ የመንግስት መ/ቤቶች የስራ ሃላፊዎች ይህንን ግንኙነት በግልፅ በማሳወቅ የዉሉ ግዴታ እስከሚጠናቀቅ በዚህ የግዢ ሂደት ዉስጥ በማንኛዉም ደረጃ ከመሳተፍ ራሳቸዉን ሳያገሉ ከቀሩ፣

በመሬት አስተዳደር ተቋማት ያሉ አመራርና ፈጻሚዎች ባለጉዳዮች በራሳቸው ይዞታ ላይ ለማልማት በግል አሰርተው ያቀረቡትን የንድፈ ሃሳብ እቅድ (ፕሮፖዛል) ያለመቀበል እና አመራሩና ባለሙያዎቹ በሚፈልጉትት አካል ወይም ድርጅት እንዲሰራ ተጽዕኖ መፍጠር፣ በግንባታ ፈቃድ የሚቀርቡ ንድፎች /ዲዛይኖች/ የክፍሉ አመራርና ባለሙያዎች በሚፈልጉትት አካል ወይም ድርጅት ካልተሰራ ተደጋጋሚ እርማት በመስጠት የባለጉዳዩን ምልልስ በማብዛት ለድርድር መጋበዝ፣ ለውጭ አማካሪ ድርጅት በመስጠት በሚሰሩ ስራዎች ላይ አመራሩ ወይም ባለሙያው ድርሻ ያለበት ድርጅት እንዲያሸንፍ ቅድመ ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

የሰራተኛ ቅጥር ሲፈፀም፤ የደረጃ እድገት ሲሰጥ እና በአጠቃላይ በሰዉ ሃብት ስምሪት ጉዳይ ላይ በሃላፊዎችና በኮሚቴ አባላት በሆኑ ሰራተኞች የሚሰጡ ዉሳኔዎች ሲያጋጥሙ የግል ጥቅምን ማዕከል ያደረጉ ፍትሃዊ ዉሳኔ የሚያዛቡ ሁኔታዎች ሲኖሩ፣

**የቡድን መወያያ ጥያቄዎች**

- ከዚህ በታች የቀረቡትን ሁለት የቡድን መወያያ ጥያቄዎች ከተረዳችሁ በኋላ የጥቅም ግጭት በምን መልክ ሊታይ ይችላል ?

ለገቢዎች ባለስልጣን የግብር ሰነዶቻቸውን ያቀረቡ አንዳንድ ነጋዴዎችን፣ የስራ ኃላፊውና ሂሳብ ሰነዶቻቸውን በባለሙያ እንዲያሰሩ ይመክሯቸዋል፡፡ ከፈለጉና ፍቃደኛ ከሆኑ ባለሙያ ሊጠቁሟቸው እንደሚችሉ ይነግሯቸዋል፡፡ አንዳንዶች ፍቃደኝነታቸውን በመግለፅ የስራ ኃላፊው የጠቆሟቸውን ባለሙያዎች አድራሻ ይቀበላሉ፡፡

የአንድ መ/ቤት የሰው ኃይል ባለሙያ በአንድ ወቅት ውለታ የዋሉላቸውን ሰው በመስሪያ ቤታቸው ያገኟቸዋል፡፡ ቀድሞ ያደረጉላቸው ውለታን ያስተውሷቸዋል፡፡ በማስተወስ እጅግ የላቀ ምስጋና በማቅረብ ለምን እንደመጡ ሲጠይቋቸው ድርጅታቸው ባወጣው የስራ ቦታ ልጃቸውን ለማስመዝገብ እንደሆነ ይነግሯቸዋል፡፡ በዚህም ባለሙያው ግድ የለም እኔ አስመዘግበዋለሁ እርሶ ይሂዱ ብለው በአክብሮት ያሰናብቷቸዋል፡፡

## 1.10 የጥቅም ግጭት የሚያስከትለው ጉዳት

**ማነቃቂያ ጥያቄዎች**

1. የጥቅም ግጭት መከላከል አስፈላጊ ጉዳይ ነው ብለው ያምናሉ? ለምን?
2. የጥቅም ግጭት (በግለሰብ፣ በማህበረሰብ፣ በተቋምና በሃገር ደረጃ) ያስከትላል የምትሏቸውን ጉዳቶች ዘርዝሩ?

የጥቅም ግጭት በይበልጥ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተሰጣቸውን ስልጣንና ኃላፊነትን የሙያ ስነምግባርን እና ህግና አሰራርን በተቃረነ መንገድ ለራሳቸው ወይም ለሌሎች ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማስገኘት ከመስራትም በተጨማሪ አንዳንድ ጊዜ ጥቅም ግጭት ለመፈጸም የሚያመቹ ህጎችንና ስርአቶችን በመቀየስ ለድርጊቶቹ ህጋዊ ሽፋን እንዲኖራቸው የማድረግ ስራን የሚሰራበት ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፡፡ በእነዚህ መንገዶች የጥቅም ግጭት ተግባራት በተበራከቱ እና ስር እየሰደዱ በሄዱ ቁጥር በግለሰቦች መብት፣ በህዝብና በሃገር ጥቅም ደረጃ (ለምሳሌ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ወዘተ..) የሚያደርሱት ጉዳት እጅግ ከፍተኛ፣ ዘርፈ ብዙ እና መጠነ ሰፊ ይሆናል፡፡

በጥቅም ግጭት ምክንያት የሚደርሱ ጉዳቶች በተለያዩ መልኩ ሊቀርቡ ይችላሉ፤ <u>**ለዚህ ሞጁል**</u> የሚከተሉት ፍሬ ሃሳቦች በምሳሌነት ቀርበዋል፡፡

- የመንግስትና የህዝብ ገንዘብና ሀብት ለታለመለት የልማት ስራዎች እንዳይውል በማድረግ ይልቁንም ግለሰቦች ተገቢና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ በመንግስት ሃብትና ንብረት እንዲበለጽጉ ያደርጋል፡፡
- ፍትሃዊና ሚዛናዊ አሰራር ስርዓትን በማዛባት የዳበረ የስራና የንግድ የዉድድር ስርዓትን ያዛባል፣
- በህጋዊ መንገድ እና በጠንካራ የሙያና የስራ ስነ-ምግባር በሚገኝ የገቢ ምንጭ የተመሰረተ የአኗኗር ስርዓትን በማዛባት፣ የሰዎች ማህበራዊ የህይወትና የኑሮ እና እድገት ደረጃ ተመጣጣኝ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡
- የነፃ ገበያ ስርዓትን በማዛባት፣ የኢንቨስትመንትና የልማት ስራዎችን በማደናቀፍ ፣ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ዕቅዶች የተዛቡና የስራዎች (በጊዜና ሆነ በጥራት) ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡
- የፍትሃዊ አሰራሮች ( በፍትህ ስረዓቱ፣ በፍርድ ቤቶች፣ በፖሊስ፣ በዓቃቤ ህግጋን አሰራሮች) እና ስርዓቶች የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን በእጅጉ ይጎዳል፣
- የመንግስት ተቋማት አሰራር እና ብሎም የአስተዳደሩ ስርዓት በአጠቃላይ የህዝብ አመኔታ እንዳይኖረው በማድረግ የዜጎች እና የመንግስትን ግንኙነት ያሻክራል፣ይሸረሽራል / lose of integrity/
- ችግሩ እልባት ሳያገኝ እየተባባሰ ከሄደ ውሎ አድሮም/ በሂደት የሃገር ሰላምና ፀጥታን እንዲቃወስ በማድረግ ሀገር እንዳይረጋጋ በማድረግ ረገድ የራሱ የሆነ አሉታዊ አንድምታ ይኖረዋል፡፡
- የማህበራዊ ተቋማት የመልካም አስተዳደር ስርዓትን በማዛባት እና የስራ ባህልን በመሸርሸር ጥራት የጎደለው የጤናና የትምህርት ስርዓትና አገልግሎት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄ

የሚከተሉትን ዝርዝር ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ በማየት የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ ጉዳዮች መሆን አለመሆናቸውን በመለየት ካስቀመጣችሁ በኋላ ለምን እንደመረጣችሁ ማብራሪያ ስጡ፡፡

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባራት | ነው | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1 | የግል ደርጅት የስራ ኃላፊ በአንድ የስራ መደብ ቦታው የሚጠይቀውን በቂ ትምህርትና ልምድ የሌለውን ዘመዱን ቅጥር ፈፀመ፡፡ | | |
| 2 | ተቀጥረው ከሚሰሩበት ተቋም ተመሳሳይነት ያለው ስራን የሚሰራ ድርጅት ማቋቋም (ለምሳሌ አማካሪ፣ የግንባታ፣ ኮንስትራክሽ ስራ የሚሰራ፣ የህትመት፣ ህክምና አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት) | | |
| 3 | ከባለድርሻ አካላትና ከአቅራቢ ደንበኛ ለወደፊት በድርጅቶቹ ውስጥ የግል ስራ ለማመቻቸት የሚደረግ ጥረት፣ | | |
| 4 | በእረፍት ጊዜና ወቅት በተቋማት ደንበኛ ድርጅት ውስጥ በአመት ፍቃድ የስራ ቅጥር ማመቻቸትና መስራት፣ | | |
| 5 | የሚሰሩበትን ተቋም ምሲጢር አሳለፎ ለመስጠት ክፍያ መቀበል፣ | | |
| 6 | የስራ ባልደረባን፣ ጓደኛን እና አብሮ የሚሰራን ባለሙ ጥፋት መመርመር አለመፈለግ ወይም ለመሳተፍ ፍቃደኛ አለመሆን | | |
| 7 | የቀጣሪ ድርጅትን ሚስጢራዊ መረጃ ለተወዳዳሪ ድርጅት አሳልፎ መስጠት፣ | | |
| 8 | ከበላይ ተቆጣጣሪ ኃላፊ ጋር የፍቅር ግንኙነት ማድረግ ወይም ለዚህ መሰል ተግባር ቀጠሮ መያዝ፣ | | |
| 9 | የራስ የግል ድርጅት ትርፍ እንዲያገኝ ከሚሰሩበት ተቋም ግዥ መፈፀም፣ ወይም ድርጅቱን ተመራጭ ማድረግ | | |
| 10 | ለሚሰሩበት ተቋም/ ድርጅት እቃ ከሚያቀርብሎት ተቋም ጋር ንግድ ሽርክና መፈፀም፣ | | |
| 11 | የቅርብ ዘመድ እንዲሁም ጓደኛ ለሆነ የበላይ ተቆጣጣሪ ሪፖርት ማቅረብ፣ | | |
| 12 | ተቀጥረው ከሚሰሩበት ተቋም ውጪ የግል ጥቅም ለማግኘት የምክር አገልግሎት ለሌላ ድርጅት በመስጠት ክፍያ መቀበል፣ | | |

## የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ የጥቅም ግጭት መሰረታዊ ሃሳቦች፣ታሪካዊ ዳራ፣የጥቅም ግጭት ምንነት፣ አይኖችን፣ገፅዎችን፣ የጥቅም ግጭትና ሙስና፣የጥቅም ግጭት መከላከል አስፈላጊነትን፣የጥቅም ግጭት መስኤዎችን፣ የጥቅም ግጭት የሚፈፀምባቸዉ መንገዶች፣የጥቅም ግጭት ተጋላጭ የሆኑ የስራ ዘርፎችንና አሰራሮችን፣ የጥቅም ግጭት ጉዳትን በዝርዝርና በጥልቀት በመዳሰስ የሚከተሉትን ሀሳቦች በማስፈር በማጠቃለል ተቀምጧል፡፡

የጥቅም ግጭት ማለት በግል እና በህዝብ ጥቅም መካከል የሚፈጠር ግጭት ነው፡፡ የጥቅም ግጭት የመንግስት ባለስልጣናት እና ሠራተኞች የግል ጥቅም እና ፍላጎት የህዝብ ጥቅምን እንዲስጠብቁ በተሰጣቸው በመንግሥት ሃላፊነት፣ተግባር እና ውሳኔያቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በሚያሳድር መልኩ አይሎ ሲገኝ በግል እና በህዝብ ጥቅም መካከል የሚፈጠር ግጭት ነው፡፡

የጥቅም ግጭት በማንኛውም የመንግስት አሰራርና ውሳኔ አሰጣጥ ሁኔታዎች ውስጥ የሚኖሩና የሚፈጠሩ ቢሆኑም በሁሉም የስራ አካባቢዎች እና ዘርፎች በተመሳሳይ ደረጃ፣ዓይነት እና መጠን ይስተዋላሉ ማለት ግን አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የጥቅም ግጭት እና ሙስና መነሻ ምክንያቶች ወይም መንስኤዎች፣ በአፈጻጸም ሂደታቸው፣ በመንግስትና ህዝብ ሃብትና ጥቅም ላይ ሊያደርሱት በሚችሉት ጉዳት፣ እንዲሁም በመከላከያ ስልቶቻቸው ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

## ምእራፍ ሁለት

## የጥቅም ግጭትን መከላከልና ማስተዳደር ስልቶች

### መግቢያ

በዓለም፣በሀገራችንና በከተማችን የጥቅም ግጭት አሳሳቢ ጉዳይ እየሆነ በመምጣቱ ምክንያት ችግሩን ለመከላከልና ለማስተዳደር ፈርጀ ብዙ ስራዎች ሲቀየሱ ይስተዋላል፡፡ በሃገራችንም የጥቅም ግጭት ከጊዜ ወደ ጊዜ በመንግስት ተቋማትና አገልግሎት ሰጭ መስሪያ ቤቶች አሳሳቢ ችግር እና ስጋት እየሆነ መጥቷል፡፡ የጥቅም ግጭት ሁኔታዎች በአግባቡ ካልተለዩ የመከላከልና የማስተዳደር ስራ ካልተሰራ የተቋማት ተአማኒነትና ህዝባዊ ተቀባይነት በመሸርሸር ለሙስና መከሰት መንስኤ ይሆናል፡፡

የመንግስት ተቋማት በተገልጋዩ ማህበረሰብ ዘንድ አመኔታና ተቀባይነት እንዲኖራቸው አገልግሎት አሰጣጣቸውና ውሳኔያቸው የማህበረሰቡን ፍላጎት እና ጥቅም ያስጠበቀና ያስቀደመ እንዲሆን

ይጠበቃል። ይህን መሰረታዊ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ኃላፊነትና መርህ ከሚሸረሽሩ ጉዳዮች አንዱ የጥቅም ግጭት እየሆነ መምጣቱ በግልፅ ይስተዋላል። በተለያዩ ጥናቶችም የተረጋገጠ ነው።

በእነዚህ ዓለም አቀፍና ሃገራዊ ገፅታዎቹና ተፅዕኖዎቹ የተነሳ ጥቅም ግጭትን በአግባቡ መከላከልና ማስተዳደር ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ በመሆኑ፣ ችግሩን ለመካላከልና ለማስተዳደር በተለያዩ ሃገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተለየዩ/ በርካታ የመከላከያ ስልቶች እየተቀየሱ ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ።

በዚህ ምዕራፍም በተለያዩ ሃገራት እንዲሁም በሃገራችን ኢትዮጵያ የጥቅም ግጭት ለመከላከል እና ለማስተዳደር የሚስችሉ ስልቶችን ይቀርባሉ። በዚሁ ምዕራፍ የተቀየሱ ስልቶችን፣ አተገባበርና አፈፃጸም ሂደት ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች ይቀርባሉ።

የምዕራፉ ዓላማ፡- ሰልጣኞች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኂላ፤-

- በአለም አቀፍ ደረጃ የሚመከሩ የጥቅም ግጭት መከላከያ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፣
- በሀገራችን የተዘረጉ የተለያዩ የጥቅም ግጭት ስልቶችና ህጋዊ ስርዓቶችን ያብራራሉ፣
- በጥቅም ግጭት መከላከል ዉጤታማነት ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን ያስረዳሉ።
- የጥቅም ግጭትን ለመከላከልና ለማስተዳደር የወጡ ህጎችን ይዘረዝራሉ፣
- የጥቅም ግጭትን ለመከላከልና ለማስተዳደር የሌሎች ሃገሮችን ልምድ ከሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ያነጻጽራሉ::
- ካገኙት ግንዛቤ በመነሳት በተቋማቸው ውስጥ የሌሎችን ሃገራት ተሞክሮ የመተግበር አቅማቸውን ያሳድጋሉ።

**የማሠልጠኛ ዘዴዎች**

- ገለጻ፤
- የጥንድና የቡድን ውይይት፣
- አስረጅ ጥናት፣
- ልምድ ልውውጥ፤

**የመርጃ መሣሪያዎች**

- ፓወር ፖይንት፤
- ማርከር፤
- ፍሊፕቻርት፣
- ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች (ስፖት፣ ድራማ).....

**የሚወስደዉ ጊዜ** 5:00 ሰዓት

## 2.1. የውጭ ሃገራት ተሞክሮዎች

***የማነቃቂያ ጥያቄዎች***

- ➢ *የተቋማችሁን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ በተቋማችሁ የጥቅም ግጭትን ለመከላከልና ለማስተዳደር በተግባር እየተሰራባቸው ያሉ ህጎችና የተዘረጉ አሰራሮችን ግለፁ፡፡ ከሌለ ለምን?*
- ➢ *የጥቅም ግጭትን በመከላከል ረገድ የተሻሉና ልምድ ሊወሰድባቸው የምንችላቸውን ሃገራት በመጥቀስ ተሞክሮ ወይም ልምድ ሊወስዱባቸው የሚችሉ ጉዳዮችን ግለጹ/ አብራሩ፡፡ በተጨባጭ ይኖራል?*

በአሁኑ ዘመን እና ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ የጥቅም ግጭትን ለመከላከል ከፍተኛ ትኩረት እየተሰጠው የሚገኝ ጉዳይ ሆኖ ይስተዋላል፡፡ በዚህ ረገድ በጥቅም ግጭት ምክንያት የሚከሰተውን ችግር ለመከላከል የዓለም ሃገራት በግላቸው ወይም በተናጠል ከሚያደርጓቸው ጥረቶች በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ በትብብር የሚሰሯቸው ስራዎች በርካታ ናቸው፡፡ ይህ የጥቅም ግጭት ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎች በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የሙስና ተግባራትን ከመከላከል ተግባራት ጋር ተጣምረው የሚታዩባቸው ሁኔታዎችና አዝማሚያዎች አሉ፡፡

ሀገራት የጥቅም ግጭትን ለመከላከልና ለማስተዳደር ያላቸውን ታሪካዊ፣ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ሁኔታቸውን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ዘዴዎች ይከተላሉ፡፡ አብዘኛቹ ሀገራት የጥቅም ግጭትን ለመከላከልና ለማስተዳደር የሚያደርጉት የተለያዩ መከላከያ ስልቶችን የሃገራቸው የፖሊሲ አካል በማድረግ ስራ ላይ ሲያውሉ ይስተዋላል፡፡

እነዚሁ ሃገራት የጥቅም ግጭትን ችግር ለመከላከል የተለያዩ የሙስና መታገያ ስልቶችን ተግባራዊ በማድረግ እና የስነ-ምግባር ግንባታ ስራዎችን መሰረታዊ የማድረግ ጠንካራ ስርዓት በመዘርጋት ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የጥቅም ግጭትን በሚመለከት በአለም አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ሃገራት የሚሰሩ እና በሃገራችንም እየተሰሩ የሚገኙ ተሞክሮዎች በሚከተለው መልክ ቀርበዋል፡፡

**ካናዳ**

ካናዳ የሥነ-ምግባር ደረጃዎችን በመንግስት ከፍተኛ ስልጣን እና ኃላፊነት ደረጃ በላቀ ሁኔታ ለመጠበቅ ወጥነት፣ ተቋማዊ እና ዘላቂነት ያለው (በመርህ ላይ የተመሠረተ) ሥርዓትን የሚያጎለብት የስነ-ምግባር ኮዶች እና መመሪያዎችን አዘጋጅታለች፡፡ ይህ የካናዳ ስርዓት ዝርዝር

ሕጎችን ከማውጣት ይልቅ በመርሆዎች ላይ በመመርኮዝ ሰፊና ግልጽ የስነ-ምግባር ደረጃዎችን በማውጣት ስራ ላይ ትኩረት ያደረገ ነዉ፡፡

ይህ አስተሳሰብ መርህ ተኮር የሚል ሲሆን የዚህ አስተሳሰብ ቀዳሚና ዋና ግብ የስራ ኃላፊዎችንና ባለሙያዎችን ስብዕናን በመገንባት የተሰጠ ኃላፊነትን በመወጣት እና አገልግሎት አሰጣጥ ግልፅነትንና ውሳኔዎች ስነ-ምግባራዊ የተላበሱ ማድረግ ነው፡፡ የዚህ ሁሉ ስራዎች መሰረታዊ ግምት ዜጎች ከግል ፍላጎታቸዉ አስቀድመዉ የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ወይም ለማሳካት ፍላጎት እንዲያድርባቸዉ ያስችላል፡፡

ካናዳ ከላይ ከተጠቀሰው አጠቃላይ መርህ ተኮር የመከላከያ ስልቶች በተጨማሪ የመንግስት ሰራተኞችን የጥቅም ግጭት መከላከልን በሚመለከት የመንግስት ሠራተኛ ከተቀጠረ በኋላ ጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚያሰችል (post employement code for public office) መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ የጥቅም ግጭትን ለመከላከለል ከምትከተላቸዉ መርህ ተኮር አካሄዶች ዉስጥ የሚጠቀስ ነዉ፡፡

## ኢንዶኔዥያ

የኢንዶኔዥያ መንግስት የጥቅም ግጭትን ለመከላከልና ለማስተዳደር የተዘረጋው ስርዓት በርካታ የህግ ማዕቀፎችንና ደንቦችን መሰረት በማድረግ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በመንግስት አስተዳደር ውስጥ የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የህዝብ አማካሪ ህግ፣ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በክልል ተወካዮች ምክር ቤት የወጣ የጥቅም ግጭት መከላከል ህግ፣ መመሪያዎች፣ የአስተዳደር ማሻሻያና የቢሮክራሲያዊ ማሻሻያ ደንቦች የጥቅም ግጭትን ለመከላከል ከወጡት የህግ ማዕቀፎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በተጨማሪም የጥቅም ግጭት ለመከላከል የወጡት የህግ ማዕቀፎች አተገባበር ላይ የሚደረገው ቁጥጥር ለማከናወንና ስርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ የመንግስት የፋይናንስና ልማት ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ፣ ኦዲተር ጀኔራል እና ሌሎች የመንግስት ተቋማት መደገፍ እንዳለባቸው የሃገሪቱ ህግ ይደነግጋል፡፡

ለምሳሌ፡- በKPK Corruption Eradication Commission (Indonesia) የፀረ ሙስና ኤጀንሲ የጥቅም ግጭቶችን በመከላከል ስራዎች በአርአያነት የሚጠቀስ ተቋም ነው፡፡ ኮሚሽኑ የሥነ-ምግባር ደንብ በማዘጋጀት ለሠራተኞችና በተቋም ሃላፊዎች ላይ የሚነሱ ሁሉንም የጥቅም ግጭት ቅሬታዎች የሚያስተናግድ የውስጥ ክትትል መምሪያ እና ስርዓት ዘርግቷል፡፡

**ደቡብ አፍሪካ**

በደቡብ አፍሪካ ህግን መሰረት በማድረግ የጥቅም ግጭትን መከላከያ ከሚከተሉ ሀገራት ዉስጥ የምትካተት ሲሆን በህገ-መንግስቱ ውስጥ የመንግስት አስተዳደር መሰረታዊ እሴቶች እና መርሆዎችን ደንግጋለች፡፡ የመንግስት አገልግሎቶችን ገለልተኛ፣ ፍትሀዊ፣ እኩልነትን እና አድሎ በሌለበት እንዲሰጥና አስተዳደሩም ተጠያቂ መሆን እንዳለበት በአስገዳጅነት ተደንግጓል፡፡

ከዚህ በመነሳት ደቡብ አፍሪካ የምትከተለዉን ህግን መሰረት ያደረገ የጥቅም ግጭት መከላከያ መርህን ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ህጎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን እና የአሰራር አደረጃጀቶችን በመፍጠር ተግባራዊ ታደርጋለች፡፡ ለአብነትም የጥቅም ግጭትን ለመከላከል ከወጡት ህጎች ጥቂቶቹ የመንግስት የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ህግ፣ ህግ-መንግሰቱ ውስጥ የተካተተው የጥቅም ግጭት መከላከል ህግ እና የመንግስት ሰራተኞች  የስነ-ምግባር ኮድ የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡

**የቡድን መወያያ ጥያቄዎች**

1. ከቀረቡት ሀገራት ተሞክሮና የሃገራችንን ትግበራ በማነጻጸር የትኛውን የጥቅም ግጭት መከላከያ ስልት ብንጠቀም ውጤታማ ሊያደርገን ይችላል ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምን?
2. በሃገራችን የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የትኞቹን ሃገራት ተሞክሮ ብንከተል የተሻለ ይሆናል ትላላችሁ?

## 2.2 በዓለም አቀፍ የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር ዘዴዎች

***ማነቃቂያ ጥያቄዎች***

1. የጥቅም ግጭትን ለመከላከልና ለማስተዳደር ምን ዓይነት ስልቶች ሊተገበሩ ይገባል ትላላችሁ? ለምን?
2. በሃገራችንስ የጥቅም ግጭት መከላከያ መንገዶች አሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? ካሉ ዘርዝሯቸው ወይም ጥቀሷቸው?

በአሁኑ ዘመን በብዙ ሃገራት ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን መከላከልን መሰረት አድርገው  ድጋፍ የሚደርጉ ዓለምአቀፍ ድርጅቶች በይበልጥ አዳጊ ሃገራት የጥቅም ግጭትን የሚከላከል ስርዓትን እና አሰራርን እንዲቀይሱ ከፍተኛ ድጋፍና የትብብር ስራዎችን ይሰራሉ፡፡

በዓለም ላይ የተቀየሱ እና ተግባራዊ እየተደረጉ የሚገኙ የጥቅም ግጭት መከላከያ ስልቶች ከሆኑት መካከል በሁለት ዓይነት መንገድ ተከፍለው ይታያሉ፡፡ እነዚህም መርህ ተኮር/ principle based/

እና ህግ ተኮር / rule based / ተከፍለው የሚታዩ ይሆናል፡፡ የተወሰኑ ሃገራት ሃገራችንን ጨምሮ ሁለቱንም ስልቶች አጣምረው ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

በተለያዩ ሀገራት ደረጃ የሚተገበሩት እነዚህ ሁለት የመከላከያ ስልቶች በሚከተሉት መንገድ ቀርበዋል፡፡

1. **መርህ ተኮር**/ principle based/ ይህ ስልት የጥቅም ግጭት ችግሮችንና ክስተቶችን በቀጥታ በተዘረጋ ህግና ስርዓት ሳይሆን የመንግስት ባለስልጣናት፣ ሙያተኞች፣ እንዲሁም በተለያ ዘርፎች የተሰማሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ከፍተኛ እና የላቀ የስነ-ምግባር ደረጃ ላይ እንዲገኙ የማድረጊያ ስራዎችን መስራትን የሚመለከት ነው፡፡

ይህ የጥቅም ግጭት መከላከያና መቆጣጠሪያ ስልት ትኩረት የሚያደርገው የቅድመ መከላከልና የመቆጣጠር ተግባር ላይ ነው፡፡ በተለይም ከስልጠና እና ከአቅም ግንባታ ስራዎች ጋር በተያያዘ የስነምግባር መርሆችን መሰረት በማድረግ የህዝብን አመኔታ የሚያጎለብቱ ተቋማትን ፣ አመራሮችንና ሰራተኞችን ተቋማዊ ባህሪ እና ስብዕና ግንባታ ላይ ነው፡፡ ጠንካራ ሞራላዊና ስነምግባራዊ በጎ ተፅእኖ የሚዳብሩና የሚጎለብቱ የስነምግባር ህግጋትና ስርዓት ማስፈን ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

በአብዛኛው ይህን መንገድ ለጥቅም ግጭት መከላከያ የሚጠቀሙ ሀገራት ገፅታ፣ የዳበ ዴሞክራሲ ስርዓትን ላይ የሚገኙ፣ በረጅም ጊዜያት ሂደት ችግሩን ለመከላከል ሰፊ ስራዎችን የሰሩ፣ የዳበረ የመከላከል ስርዓት የዘረጉና የሙስናና የጥቅም ግጭትን ጨምሮ ያላቸው ተጋላጭነት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያደረሱና መከላከል የቻሉ ሀገራት ሆነው ይስተዋላሉ፡፡ ለአብነት ያህል ካናዳ፣ እንግሊዚ፣ አውስትራሊያ ወዘተ፡፡

መርህ ተኮር በተቋማት ደረጃም የጥቅም ግጭትን እንዴት መከላከል እንደሚቻል አቅጣጫ ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ በተቋም ደረጃም ለጥቅም ግጭት የሚዳርጉ ማሳያዎችን በጥናት መለየት፤ መመዝገብ፣ በጥናት በተለዩ የአሰራሮች ላይ መረጃ በመሰብሰብ፣ በመተንተን የጥቅም ግጭት መከሰት ስጋት ተጋላጭነት ደረጃ ማውጣትና የተጋላጭነት ደረጃ የወጣላቸውን አሰራሮች ላይ የመከላከያ ስልቶችን መቀየስ ላይም የሚያተኩር ነው፡፡

2. **ህግ ተኮር** / rule based/:- የዚህ መርህ ተከታዮች ቀዳሚ መገለጫ የጥቅም ግጭትን ለመከላከል አስገዳጅ የሆኑ ህግ ስርዓቶችን በመዘርጋት እንዲሁም ህጎችን በማውጣትና ድንጋጌዎችን በማዘጋጀት ችግሩን በቀጥታ ለፍትህ አካል በማቅረብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ይህ አሰራርና ፍልስፍና ከመርህ ተኮር የሚለይበት በተለያዩ የስራ፣ የኃላፊነትና የሙያ ስነ-ምግባር ስራዎችና/ አውታሮች አማካኝት ቀድሞ የመከላከል ስርዓትን ከማጠናከር ይልቅ፣ የጥቅም ግጭት ድርጊቱ ከተከሰተ ጉዳዩን በሚመከለተውና ስልጣን ባለው አካል አማካኝነት ( ምሳሌ ፀረ-ሙስና ተቋማት) በቀጥታ ለፍትህ አካላት የማቅረብ ስራን መስራት ላይ የተኮረ በመሆኑ ነው፡፡

ይህ መርህ የተለያዩ አለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ስምምነቶችን በመቀበል እንዲሁም በሀገራችን የተለዩ የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎችን በማውጣትና ስርዓት በመዘርጋት የሚገለፅ ነው፡፡ ይህን መርህ ከሚከተሉ ሀገራት ደቡብ አፍሪካ በቀዳሚ ምሳሌነት ትጠቀሳለች፡

**የቡድን መወያያ ጥያቄዎች**

- ከሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የሚስተዋሉ መሰረታዊ የጥቅም ግጭትንም ሆነ ሌሎች ብልሹ ተግባራትን በመከላከል እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች ካሉ ዘርዝሩ? ችግሩን ለማሻሻል ምንስ መደረግ አለበት ብላችሁ ተምናላችሁ? እንዴት?

## 2.3 በሃገራችን የተቀየሱ የጥቅም ግጭትን መከላከያ ስልቶች

**ማነቃቂያ ጥያቄዎች**

1. በሃገራችን የጥቅም ግጭትን ለመከላከል ምን ዓይነት ስልቶች ሊተገበሩ ይገባል ትላላችሁ? ለምን?
2. ተቋማችሁን መሰረት በማድረግ የጥቅም ግጭት ይከላከላሉ የምትሏቸውን ስርዓቶችና አስተሳሰቦች ዘርዝሩ?

ሃገራችንን ጨምሮ ብዙ ታዳጊ ሃገራት መርህ ተኮሩን እና ህግ ተኮሩን ስልቶች አጣምረው ተግባራዊ ሲድርጉ ይስተዋላል፡፡ በዚህ መሰረት በሃገራችን የመንግስት ተቋማት የጥቅም ግጭትን በመከላከል የሚከተሉትን ስራዎች እንዲተገብሩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ ስልቶቹን ስለመተግበራቸውና ውጤት ስለማምጣታቸው ክትትል ይደረግባቸዋል፡፡

**መርህ ተኮር፡-** የተለያዩ የስነምግባር ደንቦችን በማውጣት የሙያ ስነ-ምግባር መርሆዎችና ስርዓቶች እንዲጠናከሩ በማድረግ፣ የሙያተኞች ጥምረት በማደራጀት፣ የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞችን ስነምግባር ደረጃ ለመጠበቅ የስነ-ምግባር ትምህርት የሙያ ስነ-ምባር መመሪዎችና መርሆዎች እዲጠናከሩ ዘርፈ ብዙ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፤ እየተሰሩም ይገኛል፡፡

ህግ ተኮርን በሚመለከት የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር የሚያስችሉ የተለያዩ ሃገር አቀፍ የህግ ድንጋጌዎች እንዲሁም ሀገሪቷ የፈረመቻቸውና ያፀደቀቻቻው ዓለም አቀፍና አሃጉራዊ ስምምነቶች ለህግ ተኮር ማዕቀፎች መሰረቶች ናቸው፡፡ ዋና ዋናዎቹ ህጎች በሚከተለው መንገድ ቀርበዋል፡፡ በሀገራችን ለሚከሳቱ የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከልና ለማስተዳደር የሚግዙ ሃገራዊ ህጎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

## 3.2.1 ሃገራዊ ህጎች

የ1987 ዓ.ም የኢፌዴሪ ህገ መንግስት ላይ አንቀፅ 12 ‹‹የመንግስት አሰራር እና ተጠያቂነት›› በሚለው መርህ ውስጥ የመንግስት አሰራር ለህዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይህም የግልፅነት አሰራር በተቋማት መዘርጋቱ የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚያስችል መነሻ ሀገራዊ ህግ ሆኖ ያገለግላል፡፡

አዋጅ ቁጥር 668/2002 አንቀፅ 16 ላይ የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ መወሰድ ስላለበት እርምጃ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይህም ‹‹የመንግስት ባለስልጣን ወይም ሰራተኛ ግጭት ሊያስከትልበት የሚችል ጉዳይ ሲያጋጥመው፡- በጉዳዩ ላይ ማንኛውንም ውሳኔ ወይም ድርጊት ከመፈጸም መቆጠብ እና ማሳወቅ እንዳለበት እንዲሁም የጥቅም ግጭት ሊከሰት መቻሉ የተገለጸለት ኃላፊ እንደሁኔታው ጉዳዩን ማየቱን አንዲቀጥል ወይም ሌላ ሰው ተተክቶ እንዲያየው፤ በአንቀፅ 17 ደግሞ የጥቅም ግጭት መከሰቱን ተከትሎ ስለሚወሰድ እርምጃ በተመለከተ ግጭት መከሰቱን ተከትሎ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በኃላፊው ሲጠየቅ ራሱን ከኃላፊነት የማግለል ግዴታ እንዳለበት ይገልፃል፡፡

በዚህ አዋጅ አንቀፅ 14 ላይ , እንደ መርህ ያስቀመጠውን ስንመለከት ደግሞ ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የያዘውን መንግሥታዊ የሃላፊነት ቦታ የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ ማዋል እንዳለበት ይገልፃል፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 15 ላይ ደግሞ ማንኛውም የመንግስት ሃላፊ ወይም ባለስልጣን ሥልጣኑን የሚፈታተን ወይም የጥቅም ግጭት የሚፈጥር ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ መቀበል እንደሌለበት ይደነግጋል፡፡

የተሻሻለው የሙስና ወንጀል ህግ አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 13/4- ደግሞ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ጥቅም የማግኘት ወይም የማስገኘት ሃሳብ ሳይኖረው ራሱ ወይም የቅርብ ዘመዱ ወይም የትርፍ ተካፋይ በሆነበት ወይም አባል የሆነበት የበጎ አድራጎት ድርጅት እና እሱ በሚሰራበት መስሪያ ቤት /ድርጅት መካከል በንግድ፣ በግዥ ወይም በሽያጭ ወይም በማንኛውም የስራ ግንኙነት ውል እንዲፈፀም ያደረገ

እንደሆነ በሙስና ወንጀል ፈፀሚነት ተጠያቂ እንደሚሆን ይገልፃል፡፡ ይህም የመንግስት ሃላፊዎችና ባለስልጣናት ከተሰጣቸው ሃላፊነት ውጭ ለጥቅም ግጭት የሚዳርግ ሁኔታውች ውስጥ እንዳይገቡ የሚያስጠነቅቅ ነው፡፡

የተሸሻለው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 6/5 ላይ የኮሚሽኑ ዓላማዎች ተብሎ እንደተገለፀው የመንግስት ባለስልጣናትን እና የሰራተኞችን ሃብት እና የገቢ ምንጮቻቸውን በማሳወቅ፣ በመመዝገብ፣ ተደራሽ በማድረግ፣ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ የግልፅነት እና የተጠያቂነትን ስርዓት መፍጠር ፤ በአንቀፅ 6/7 ላይ ደግሞ የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግስት ተሿሚዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና የህዝባዊ ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ከተሰጣቸው ኃላፊነት፣ ከመቆጣጠር እና ከመወሰን ስልጣን ጋር በተያያዘ የሚፈጠር የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚያስችል ስርዓት እንደሚዘረጋና የመከላከል ስራ እንደሚሰራ ይገልፃል፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ የህግ ማዕቀፎች ሳይሸራረፉ ቢተገበሩ ግልፅ በሆነ መንገድ የጥቅም ግጭትን ህግ በማውጣትን ስርዓት በመዘርጋት ለመከላከል የሚያስችሉ ናቸው፡፡

## 2.3.2 ዓለም አቀፍና አሃጉራዊ ስምምነቶች

ኢትጵያ የተቀበለቻቸው በተባበሩት መንግሰስታት ፀረ ሙስና ኮንቬንሽን አንቀፅ 7 ላይ (የህዝብ ዘርፍ) ፡- UNCAC proc 544/2007 Article 7(4):- (Public sector) - Each State Party shall, in accordance with the fundamental principles of its domestic law, endeavor to adopt, maintain and strengthen systems that promote transparency and prevent conflicts of interest.

የዚህ አንቀፅ ትርጓሜ እንደሚመላክተው የኮንቬንሽኑ አባል ሀገራት መሰረታዊ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ በየሀገሮቻቸው ህጋጋት ውስጥ ግልፅነት የሚያሳድግ እና የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚያስችል ጥረቶችን መጠበቅ፣የማጠናከር ስራዎችን የመዘርጋት ግዴታ እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ በተጨማሪም የዚህ ስምምነት ፈራሚ ሀገራት የጥቅም ግጭትን የመከላከል ስራ የሀገራት የህግ ማዕቀፍ አካል እንዲሆን የሚያሳስብ ነው፡፡

የአፍሪካ ሕብረት የፀረ-ሙስና መከላከያና መዋጊያ ኮንቬንሽን (AUCAC 545/2007 Article 3/3 principles, Transparency and accountability in the management of public affairs)

በሚለው አንቀፅ ውስጥ ኮንቬንሽኑ ፈራሚና አፅዳቂ ሀገራት በመንግስት የአስተዳደር ጉዳዮች ውስጥ የግልፅነትና የተጠያቂነት መርህን ተግባራዊ ማድረግ  አለባቸው በማለት ያስቀምጣል፡፡ ይህም የግልፅነት መርህን መዘርጋት የጥቅም ግጭትን ለመከላከል ፋይዳ እንዳለውና በትኩረት ሊሰራበት እናደሚገባ የሚያመላክት ነው፡፡

### 2.3.3 በአዋጅ 668/2002 የጥቅም ግጭትን ስለማሳወቅ እና ስለማስወገድ

የሀብትና ጥቅም ማሳወቅ እና ማስመዝገብ ህግ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የሚዳርጉ የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል እና ጤናማ በሆነ መንገድ ለማስተዳደር የሚያግዝ መሳሪያ ነው፡፡ቀጥለን በአዋጅ 668/2002 ውስጥ የጥቅም ግጭትን ስለማሳወቅ እና ማስመዝገብ የተደነገጉ ድንጋጌዎች እንመለከታለን፡፡

የጥቅም ግጭት የመከላከል እና የማስወገድ የህግ ማእቀፎች መሰረት የሚያደርጉት የህዝብን ጥቅም የማስቀደም መርህ ነው፡፡ የመንግሥት ባለስለጣናት ሠራተኞች የተሰጣቸውን ተግባር እና ሃላፊነት ማዋል ያለባቸው የህዝቡን ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ እንጂ የግላቸውን፣ የቤተሰባቸውን ወይም የወዳጆቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ማዋል እንዳለባቸው፡፡የሚገልጽ መርህ በአዋጁ አንቀጽ 14 መርህ በሚል ርእስ ተገልቷል፡፡

የጥቅም ግጭትን የማሳወቅ እና የማስወገድ መርህን አስመልክቶ‹‹ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ የያዘውን መንግስታዊ የኃላፊነት ቦታ የህዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ ማዋል አለበት፡፡ በማንኛውም ምክንያት ቢሆን በሥራው አጋጣሚ ያገኘውን እና ህዘብ እንዲያውቀው ያልተደረገን መረጃ ለግል ጥቅም ማዋል እንደሌለበት›› በአዋጁ አንቀፅ 14 ተገልጸል፡፡

የጥቅም ግጭት ለመከላከል ሊወሰዱ ከሚገቡ እርምጃዎች መካከል በውሳኔ ላይ ተጽእኖ ሊያደርጉ እና ለጥቅም ግጭት ሊዳድርጉ የሚችሉ ሁኔታዎች ማስወገድ አንዱ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ለጥቅም ግጭት ከሚያጋልጡ ሁኔታዎች መካከል ስጦታ፣መስተንግዶ እና ግብዣን የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡እነዚህ ጉዳዮች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ በማሳደር የጥቅም ግጭት መንስኤ ይሆናሉ፡፡ከዚህ አንጻር አዋጁ ስጦታ፣መስተንግዶ እና የጉዞግብዣን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 15 /1/ ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የመወሰን ሥልጣኑን የሚፈታተን ወይም የጥቅም ግጭት የሚፈጥ ርስጦታ፣መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ መቀበል እንደሌለበት ተደንግጓል፡፡

የዚህ ድንጋጌ ዋና ዓላማ የመንግሥት ሠራተናው የማይገባ የውሳኔ አጣብቅኝ ወይም የጥቅም ግጭት ውስጥ እንዳይገባ ከመጀመሪያውኑ ለመከላከል ነው፡፡

የመንግስት ሰራተኛ በመንግስት ሰራተኛነቱ ስጦታ፣መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ ሲያቀርብለት አልቀበልም ለማለት ከፍተኛ ፈተና ውስጥ እንደሚገባ መገመት ይቻላል፡፡ ስጦታ ለሰጠውም የመወሰን እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ድንጋጌ የመንግስት ሰራተኛው የማይገባ የሕሊና ወይም የጥቅም ግጭት ውስጥ እንዳይገባ ከመጀመሪያውኑ ለመከላከል እንዲቻል ተብሎ የተደነገገ ነው፡፡

የአንቀጽ 15/1/ ድንጋጌ ተሿሚው፣ ተመራጩ ወይም የመንግስት ሠራተኛው ማንኛውንም ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም ግብዣ ጨርሶ እንዳይቀበል አይከለክልም፡፡መቀበል የማይቻልን ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም ግብዣ ሕጉ ለይቶ አስቀምጧል፡፡ በአንቀጹ 15/1/ እንደ ተገለጸው መቀበል የሚከለክለው የመወሰን ስልጣንን የሚፈታተን ወይም የጥቅም ግጭት የሚፈጥር ስጦታ መስተንግዶ ወይም ግብዣ ብቻ ነው፡፡ የመወሰን ስልጣንን የሚፈታተን ወይም የጥቅም ግጭት የማይፈጥር ስጦታ፣መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ መቀበል አልተከለከለም ማለት ነው፡፡

በአንቀጽ 15/1/ ስልጣንን የሚፈታተን ወይም የጥቅም ግጭት የሚፈጥር ስጦታ፣መስተንግዶ ወይም ግብዣ የተከለከለ ቢሆንም፤ ተሿሚው፣ ተመራጩ ወይም የመንግስት ሠራተኛው የቀረበለትን ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ ያለመቀበል፤ በስራ ግንኙነት ላይ ጉደት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ስጦታውን፣ መስተንግዶውን ወይም የጉዞ ግብዣውን መቀበል እንደሚችል፤ሆኖም የተቀበለውንም ስጦታ አግባብ ላለው የመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት ገቢ ማድረግ ወይም መስተንግዶውን ወይም የጉዞ ግብዣውን ለኮሚሽኑ ወይም አግባብ ላለው የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ማሳወቅ እንዳለበት በአዋጁ አንቀፅ 15/2/ ተደንግጓል፡፡

ስጦታው የመወሰን ሥልጣኑን የማይፈታተን እና የጥቅም ግጭት የማይፈጥር መሆኑን እንዴት ማወቅ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የመንግሥት ሠራተኛው ከወንድሙ ወይም ከዘመዱ ለዓመት በዓል ሙክት በግ ወይም የወርቅ ሃብል በስጦታ መልክ ቢበረከትለት ከተሰማራበት የሥራ ዘርፍ ጋር የተገናኘ ስጦታ ባለመሆኑ መቀበል ይችላል?

የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ ከሚችሉባቸው ጉዳዮች መካከል ተሿሚ፣ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ በሥራ ሃላፊነቱ የራሱ ወይም የቅርብ ዘመዱ ጥቅም ባለበት ጉዳይ የመወሰን አጋጣሚ ወይም ሁኔታ ሲፈጠር አንዱ ነው፡፡

ተሿሚ፣ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ በሥራ ሃላፊነቱ እና በራሱ ወይም በቅርብ ዘመዱ መካከል የጥቅም ግጭት የሚፈጥር ሁኔታዎች ሲገጥመው የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ ምን ማድረግ አለበት?

በአዋጁ አንቀጽ 16 የጥቅም ግጭት ሊያስከትል የሚችል ጉዳይ ሲያጋጥመው፡-የጥቅም ግጭቱን ለማስወገድ መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች የሚከተሉት ተደንግገዋል፡፡

ተሿሚው፣ ተመራጩ ወይም የመንግስት ሠራተኛው በመንግስት የሥራ ኃላፊነቱ እና በራሱ ወይም በቅርብ ዘመዱ የግል ጥቅም መካከል ግጭት ሊያስከትል የሚችል ጉዳይ ሲያጋጥመው በጉዳዩ ላይ አስተያየት ወይም ውሳኔ ከመስጠት እንዲሁም ከኃላፊነቱ ጋር የማይጣጣም ወይም ታማኝነቱን ጥርጣሬ ውስጥ የሚጥል ማንኛውንም ድርጊት ከመፈፀም መቆጠብ እንዳለበት በአዋጁ አንቀፅ 16(1)(ሀ)ሲገለጽ፤ሁኔታውን ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ማሳወቅ እንደለበት በአዋጁ አንቀፅ 16(1)(ለ)) ተደንግጓል፡፡ ይህን ያወቀ የበላይ ኃላፊም እንደሁኔታው ተ□ሚው፣ ተመራጩ ወይም የመንግስት ሠራተኛው ጉዳዩን ማየቱን እንዲቀጥል መመሪያ ሊሰጠው ወይም ሌላ ሰው ተተክቶ እንዲያየው ሊያደርግ ይችላል / የአዋጁ አንቀፅ 16/2//፡፡

በአዋጁ የቅርብ ዘመድ ማለት የተ□ሚው፣ የተመራጩ ወይም የመንግስት ሠራተኛው ወላጆችን፣ ተወላጆችን፣ እህቶችን፣ ወንድሞችን እና ሌሎች እስከ ሦስት ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ሰዎችን ያጠቃልላል፡፡ / የአዋጁ አንቀፅ 2/8//

ተሿሚው፣ ተመራጩ ወይም ሠራተኛው የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት በራሱ የሚወሰደው እርምጃ በአንቀፅ 16(1) (ሀ) እና (ለ) የተገለጹት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ተሿሚ፣ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በመንግሥት የሥራ ኃላፊነቱ እና በራሱ ወይም በቅርብ ዘመዱ የግል ጥቅም መካከል ግጭት ቢከሰት፣የጥቅም ግጭት መከሰቱን ተከትሎ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በበላይ ኃላፊው ሲጠየቅ ጥፋተኛ መሆኑን በክፍትአምኖ ይቅርታ የመጠየቅ ወይም ራሱን ከኃላፊነት የማግለል ግዴታ እንዳለበት በአዋጁ አንቀፅ 17 ላይ ተገልጿል፡፡

የጥቅም ግጭትን መከላከል ከሥራ መልቀቅ በኂላም ለተወሰኑ ዓመታት ቀጣይነት አለው፡፡ ይኸውም ተሿሚው፣ተመራጩ ወይም የመንግስት ሠራተኛው ሥራ በለቀቀ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ሲቆጣጠራቸው ከነበረው ሰዎች ጋር ጥቅም የሚያገኙ ስራዎችን መስራት እንደሌለበት በአዋጁ አንቀፅ 18 ይደነግጋል፡፡

ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ የጥቅም ግጭት መኖሩን የማሳወቅ ግዴታ ያለበት ሲሆን የጥቅም ግጭት መኖሩን በዚህ አዋጅ መሠረት የማሳወቅ ግዴታውን ካልተወጣ አግባብ ባለው የሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ እንደሚወሰድበት አንቀጽ 19 ላይ ተደንግጓል፡፡

## 2.4 የጥቅም ግጭትን በመከላከል በሃገራችን ተቋማት እየተወሰዱ ያሉ ተግባራት

***የማነቃቂያ ጥያቄዎች***

1. በሃገራችን ተቋማት የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የተዘረጉ አሰራሮች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች ካሉ ግለፁ፡፡ አተገባበራቸውስ ምን ይመስላል?
2. የስነ ምግባር ደንብ እና የሙያ ስነ ምግባር የጥቅም ግጭትን በመከላከል ረገድ ፋይዳ እንዳላቸው ታምናላችሁ? ለምን?
3. የጥቅም ግጭትን በመከላከል የሙያ ስነምግባር /ethical code /ያላቸውን አስተዋፅኦ በምሳሌነት በማንሳት አስረዱ?

በሃገራችን ከቅርብ አመታት ወዲህ የጥቅም ግጭትን ለመከላከልና ለማስተዳደር የሚደረጉ ብዙ ዓይነት ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ቀደም ሲል በምዕራፍ 2 እንደተብራራው በርካታ የሚባሉ ሃገር አቀፍ የህግ ማዕቀፎች እና ዓለምአቀፍ ስምምነቶችን ማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ክፍል ከመንግስት አጠቃላይ ፖሊሲና ስትራቴጂ ባሻገር እያንዳንዱ ተቋማት የጥቅም ግጭትን የመከላከል ስርዓት ሲቀይሱ ይስተዋላል፡፡

በይበልጥ ለጥቅም ግጭት ተጋላጭነታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተቋማትና ጥቅም ግጭት የሚከላከሉበትና የሚያስተዳድሩበት የተቀየሱና ተግባራዊ እየተደረጉ የሚገኙ የተዘረጉ ስርዓቶች የሰራተኞች ስነ-ምግባር ደንብ እና የሙያ ስነምግባር ቀዳሚ ተጠቃሽ መንገዶች ናቸው፡፡

### 2.4.1 አሰራሮችና ማንዋሎች

የፌደራል መንግሰት የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የግዢ አፈፃፀም ማንዋል የጥቅም ግጭትን በሚከተለው መልኩ መከላከል እንደሚቻል ይገልጻል፡፡

የመንግስት መ/ቤቶች በሚያወጡት ጨረታ ላይ ለመሳተፍ ከሚፈልጉ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያላቸዉ የሚመለከታቸዉ የመንግስት መ/ቤቶች የስራ ሃላፊዎች ይህንን ግንኙነት በግልፅ ማሳወቅና የዉሉ ግዴታ እስከሚጠናቀቅ በዚህ የግዢ ሂደት ዉስጥ በማንኛዉም ደረጃ ከመሳተፍ ራሳቸዉን ማግለል እንደሚኖርባቸዉ የሚጠቅስ መሆኑ፣

በአንድ ጨረታ ስፔስፊኬሽን ዝግጅት ዉስጥ የተሳተፉ ሰዎች ወይም ድርጅቶች እንዲሁም ከነዚህ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ጋር ቅርበት ያላቸዉ ሌሎች ሰዎች ወይም ድርጅቶች በተጠቀሰዉ ጨረታ ዉስጥ መሳተፍ እንደሌለባቸዉ የተመላከተ መሆኑና ሌሎች በርከት ያሉ ጉዳዮች ተጠቅሰዋል፡፡

## 2.4.2 የመንግስት ሰራተኞች ስነ-ምግባር ደንብ

በሃገር ደረጃ የሰራተኞች የስነ ምግባር ደንብ ማጠናከር ሰራተኞች ሙያቸውን አክብረው በሃቀኝነት እና በተሟላ ስብዕና ግዴታዎችንና ኃላፊነቶችን እንዲያከብሩ፣ ሊከተሏቸው፣ ሊያከብሯቸው እና ተግባራዊ ሊያደርጓቸው የሚገቡ እሴቶችን አቅጣጫ የሚያመላክትና የሚመራ መሳሪያ ነው፡፡ ከዚህም በላይ የስነምግባር መመሪያ አንዱ ዓላማ ሰራተኞች፣ ባለሙዎችና የስራ ኃላፊዎች በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የጥቅም ግጭትን እንዴት መከላከል እንደሚችሉ ወይም እንዳለባቸው የሚያስተምርና የሚያስገነዝብ ሰነድ ሆኖ ይወሰዳል፡፡

ስለዚህ ስነምግባር መመሪያ ሰራተኞች ሁሉ ለሙያቸውና ለስራቸው ታማኝ በመሆን ለግል ጥቅማቸው ሳይሆን ለህዝብ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ሃላፊነታቸውንና የሙያ ግዴታቸውን እንዲወጡ አይነተኛ ሚና ይጫዎታል፡፡

በሀገራችን ያሉ የመግስት ተቋማት የራሳቸዉ የሆነ የሰራተኞች ስነ-ምግባር ደንብ ያዎጣሉ አዋጅ 1236/13 ያስገድዳል፡፡ ለምሳሌም ከታች የተዘረዘሩ ተቋማት እንዴ ማሳያ ተቀምጠዋል፡፧

1. በኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን በተቋሙ የሰራተኞች የስነምግባር መመሪያ ላይ የሚፈጠሩ የጥቅም ግጭቶችን በመለየት በዝርዝር ያስቀመጠ መሆኑ፣

2. በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር የተቋሙ ሰራተኞች ተቋሙን ለቀዉ ከወጡ ወይም ከተሰናበቱ ለሁለት አመት ያህል ምንም አይነት የንግድ ስራዎችን ፣ ለግል ተቋማት የሂሳብ ስራዎችን እንዳይሰራ የሚያግድ መመሪያ ያለዉ መሆኑ፣

3. የፌደራል የስነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የጥቅም ግጭትን ለመከላከል በኮሚሽኑ ሠራተኞች እና ኃላፊዎች ላይ ተግባራዊ የሆነ የተቋሙ ሠራተኞች በትርፍ ሰዓት የሚሰሩት ስራ ከያዙት ሃላፊነታቸዉ ጋር የሚገናኝ ወይም የጥቅም ግጭትን ሊፈጥሩ የሚችሉ ስራዎችን በትርፍ ሰዓት እንዳይሰሩ የሚከለክል የአስተዳደር ደንብ መኖሩ፣ በሌላ በኩል ተቋማት የጥቅም ግጭት ምንነትና ከተቋሙ አንፃር የሚኖረዉን ትርጓሜ በመረዳት ይህን የማሰልጠኛ ሰነድ በማዘጋጀት ተግባር ላይ በማዋል የጥቅም ግጭትን ለመከላከልና ለማስተዳደር እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን ያመለክታል፡፡

### 2.4.3 የሙያ ስነምግባር

የሙያ ዘርፎች ለሙያዊ ስነ-ምግባር ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ እነዚሁ የትምህርት ዘርፎች የሙያ ስነ-ምግባርን አንድ የትምህርት ኮርስ አድርገው ይሰጣሉ፡፡ ከዚህም በላይ ትምህርቱን ሲያጠናቅቁ ለሙያቸው ታማኝነታቸውን የሚያረጋግጡበት ቃለ መሃላ ይፈፅማሉ፡፡ በዚህም በስራቸው ላይ ሲሰማሩ በማንኛውም ሁኔታዎች ውስጥ ህብረተሰቡን ከሚጎዱ ተግባራት እንዲሚቆጠቡ ይታመናል፡ ፡ ሙያተኞችን ለጥቅም ግጭት ከሚዳርጉ ተግባራት ራሳቸውን እንዲያርቁ አቅጣጫና ትኩረት ይሰጣል፡፡

በዚህም በተለያየ ተቋማት ውስጥ የተሰማሩ ከፍተኛና የላቀ የሙያ ዘርፍ ከሆኑት መካከል ዳኞች፣ ዓቃብያን ህጎች፣ ጠበቆች፣ ጋዜጠኞች፣ ሃኪሞች፣ መሃንዲሶች፣ መምህራን ወዘተ የጥቅም ግጭትን በማስወገድ ለሙያቸውና ለህዝቡ ታማኝ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ለአብነት ያህል የዳኞችንና የጠበቆችን የጥቅም ግጭት መከላከል የሚመለከቱ ሃሳቦች በምሳሌነት እንመልከት፡-

ዳኞች ከተከራካሪ ወገኖች እና ክርክር ከተነሳበት ጉዳይ ጋር ካላቸው ግንኙነት አንፃር እንዲሁም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት አያስችልም የሚያስብል ሁኔታዎች ሲኖር የጥቅም ግጭት ሊከሰት እንደሚችል በፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 43/94 በአንቀጽ 27 ተመልክቷል፡፡

**ለምሳሌ፡-**

ከተከራካሪ ወገኖች ጋር ባለው ግንኙነት የጥቅም ግጭት የሚፈጠረው ዳኛው ከአንደኛው ወገን ወይም ከጠበቃው ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ፣

አንድ ዳኛ በዳኝነት ከመሾሙ በፊት በጥብቅና ሙያ ተሰማርቶ እያለ ለደንበኛው የጥብቅና አገልግሎት የሰጠበት ጉዳይ በዳኝነት ከተሾመ በኂላ ዳኝነት እንዲሰጥበት ቢቀርብለት የጥቅም ግጭት እንደተከሰተ የሚቆጠር መሆኑ፣

የዓቃቢ ህግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 8/1996 በአንቀፅ 72 መሰረት ማናቸውም ዐቃቤ ሕግ የራሱ፣ የዘመዶቹ ወይም የቅርብ ወዳጆች የግል ጉዳይ ወይም ጥቅም ከስራው ወይም በስራው ምክንያት ከያዘው የህዝብ ወይም የግለሰብ ጉዳይ ጋር የተያያዘ ሆኖ ሲገኝ ይህንኑ ችግር ለበላይ ኃላፊው ወዲያውኑ በማሳወቅ ጉዳዩ በሌላ ዐቃቤ ህግ እንዲታይ ማድረግ እንዳለበት ይጠቁማል፡፡

**የቡድን መወያያ ጥያቄዎች**

በሃገራችን ከሚታየው ብልሹ አሰራሮችና የጥቅም ግጭት ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ ሁለት ዓይነት ተፃራሪ ሃሳቦች ሲንፀባረቁ ይስተዋላል፡፡ አንዳንዶች የሙያ ስነምግባር እጅግ ከፍተኛ መዳከም ላይ ይገኛል በሚል በምሳሌ ለማሳመን ይሞክራሉ፡፡ ሌሎች አካላት ደግሞ በየሙያ ዘርፉ የሙያተኛ ቁጥር ስለተበራከተ ነው እንጂ አብዛኛውን በሚባል ደረጃ የሙያ ስነምግባር የተላበሱ ናቸው፡፡ በእነዚህ ሃሳቦች መሰረት፡-

1. የትኛውን ሃሳብ ትደግፋላችሁ ለምን ምክንያታችሁን በምሳሌ በማስደገፍ አቅርቡ?
2. የሙያ ስነምግባር ከሌሎች የመንግስት ሰራተኞች ስነ-ምግባር ደንብ የሚለዩበት ሁኔታዎች ካሉ አብራሩ?
3. ከሁሉም በላቀ የሙያተኛ የጥቅም ግጭትን ሁኔታ ለመካላከልና ለማስተዳደር ሙያተኞች ላይ ለምን ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምን? ምክንያታችሁን አብራሩ፡፡
4. የአመራሩን፣ ሰራተኛውንና የሙያተኛውን ስነ-ምግባር ሁኔታ የተሻለ ደረጃ ላይ ለማድረስ ምን አይነት ስራዎች ሊሰሩ ይገባል ትላላችሁ?

## 2.5 የጥቅም ግጭት በመከላከልና በማስተዳደር መሰረታዊ ተግዳሮቶች

**ማነቃቂያ ጥያቄዎች**

1. የጥቅም ግጭትን ለመከላከልና ለማሳተዳደር መሰረታዊ ችግር ይሆናሉ ወይም ናቸው የምትሏቸውን ጉዳዮች ዘርዝሩ?
2. ተቋማችሁን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ የጥቅም ግጭት ውጤታማነት ዋና ቀዳሚ ችግሮች ምንድን ናቸው? መፍትሄ ይሆናሉ የምትሏቸውን ጉዳዮችም አብራሩ፡፡

የጥቅም ግጭት ስርዓትን ለመዘርጋትና ተግባራዊ በማድረግ ሂደት የዴሞክራሲ ስርዓት ባልበለፀገባቸው ታዳጊ ሃገራት አስቸጋሪና አዝጋሚ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ጉዳዮች በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡

ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት አለመኖር፡- ማንኛውንም ዓይነት የጥቅም ግጭት ተግባራትን ( ሌሎች ብልሹ አሰራሮችና ሙስና) ለመከላከል፣ ለመከታተል፣ ለማረም ቀዳሚ ስልጣንና ኃላፊነት ያለው አካል የመንግስት ስልጣንን የተቆጣጣጠረው ድርጅት ወይም አመራር እንደሆነ ይታወቃል፡፡ አመራር ማለት ከከፍተኛው የስልጣን አካል እስከ ታችኛው የአስተዳደርና የተቋም ደረጃ የሚሰየሙ

አመራርና ባለሙዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በተቋም የእነዚህ አካላት ቁርጠኝነት የጥቅም ግጭትን ህግና ፖሊሲ ከማውጣትና ከመተግበር አኳያ የጎላ አርዕያነት ያለው አቋምና ስብዕና ከሌለው በጥቅም ግጭት ዙሪያ ላይ ውጤታማ ስራዎችን መስራት አዳጋች ይሆናል፡፡

የግልፅነትና የተጠያቂነት አሰራር ባህል ያልተላበሰ ወይም የማይከተል የአስተዳደር ስርዓት ፣ አደረጃጀትና መዋቅር፣

የመንግስት ስልጣንና ኃላፊነትን የህዝብና የዜጎችን መብትና ጥቅም ማስከበሪያ ነው ከሚለው መርህ ባፈነገጠ ሁኔታ ፣የመንግስት ስልጣንና ኃላፊነት የግልና የሌሎችን ጥቅም ማስከበሪያ/ ማግኛ መንገድ ሆነው የሚታሰቡ መሆኑ፡፡

**የቡድን መወያያ ጥያቄዎች**

በአንድ ሃገር የህግ አውጪ አካል የጥቅም ግጭትን በመከላከያ መንገዶች ዙሪያ በቂ የሆነ አቋምና ስምምነት የለም፡፡ አንዳንድ አካላት መንግስት ፣ የመንግስት ተቋማትና አመራሮች የጥቅም ግጭት ፖሊሲ እንዲያወጡ፣ የስብዕና ግንባታ ላይ በትኩረት እንዲሰሩ፣ ተጋላጭ የስራ አካባቢዎችን በጥናት በመለየት አሰራሮችን እንዲያስተካክሉ፣ የተጠያቂነት ስርዓትን እንዲያጠናክሩ፣ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ማድረግ በቂ ነው የሚል ሃሳብን ያራምዳሉ፡ ፡ ሌላኛው ወገን ደግሞ የሚያራምደው እስካሁን የሙስናና ብልሹ ተግባራትን የሚከላከሉ ብዙ ዓይነት ህጎች ስላሉ እነዚህን ህጎች በሚገባ ተግባራዊ ማድረግና የቅጣት ደረጃቸውን ማጠናከር ብቻ ነው የሚስፈልገው የሚሉ ናቸው፡፡

ሀ. ይህ ልዩነት በሃገራችን ምክር ቤት አባላት የሚስተዋል ቢሆን በግላችሁ የትኛውን ሃሳብ ትደግፋላችሁ? ለምን?

ለ. በኢትዮጵያ ደረጃ ከእነዚህ ሃሳቦች የተለየ መተግበር የሚችሉ መከላከያ ስልቶች ናቸው የምትሏቸው ጉዳዮችን ካሉ ጥቀሱ፡፡

የሃገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴርን ጨምሮ ከፍተኛ አመራሮች የሙስናና ብልሹ ትግባራትን መከላከያ ስልቶችና የህግ ስርዓቶች በመዘርጋታቸው ለሌሎች ሃገሮች አርአያ ነን የሚል ገለፃ ለሚዲያ አካላትና የውጪ ድጋፍ ሰጪ አካላት ሳይቀር በ‹‹ኩራት›› በሚዲያና በተለያዩ መድረኮች ሲገልፁና ሲብራሩ ይስተዋላሉ፡፡ ሆኖም ብዙ የሃገራችን ሙሁራንና ዜጋው መንግስትን በጥቅም ግጭትና ሌሎች ብልሽ ተግባራትን በተመለከተ የሚያነሳው ከፍተኛ ቅሬታ ከምን የመነጨ ነው ተብለው

ለሚጠየቁት የሚሰጡት ምላሽ፤ ‹‹ ይህ ሃሳብ የተቃዋሚ ፓርቲና ስልጣን የተነፈጉ አካላት ፕሮፓጋንዳ ነው›› የሚል ነበር፡፡ ችግር ካለም በሂደት ይሻሻላል የሚል ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

ሀ. መሪዎች እንዳሉት በቂ ህግና ስርዓት ተዘርግቶ፣ ለምን ቅሬታ ሊፈጠር ይቸላል? አብራሩ፡፡ ከታዳጊ ሃገራት ነባራዊ ሁኔታዎች አኳያ ለጋሽና ድጋፍ ሰጪ አካላት የትኛውን ሃሳብ ሊያምኑ ይችላሉ / ይገባቸዋል? ምንን መሰረት አድርገው? ለምን?

## 2.6 በተቋማት ደረጃ ለሚፈፀም የጥቅም ግጭት ተግበራት መፍትሄ የሚሰጥባቸው መንገዶች

**ማነቃቂያ ጥያቄ**

1. በምትሰሩበት ተቋም የጥቅም ግጭት ድርጊት ቢፈጸም ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?
2. በአንድ ዳኛ የተፈፀመ የጥቅም ግጭት ተግባር በምን ዓይነት መንገዶች መፍትሄ ሊሰጠው ይገባል ትላላችሁ? አማራጨ መንገዶች ካሉ ዘርዝሯቸው ?

ቀደም ሲል ሲገለፅ እንደነበረው በማንኛውም ሁኔታ እና የስራ አካባቢ ውስጥ የጥቅም ግጭት ነባራዊ ሁኔታዎች እንደሚኖሩ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡ የጥቅም ግጭት አይነቶችና ተግባራትም እንዲሁ ተዘርዝረው እናገኛለን፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ ነባራዊ የጥቅም ግጭት አጋጣሚዎች ወደ መተግባር ከተፈፀሙ መፍትሄ የሚሰጥባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ፡፡ መፈጸሙም ከተረጋገጠም የተለያዩ ቅጣት ዓይነቶች ይወሰንባቸዋል፡፡

የጥቅም ግጭት ከተከሰተና ከተረጋገጠ እንደ ጥፋቱ ዓይነት እና እንደ ጥፋቱ ክብደት ፈፃሚው በሚከተለው ሁለት መንገዶች ለፍትህ ይቀርባል ብሎም ለቅጣት ይደረጋል፡፡ በየተቋማቱ እና በየሙያ ዘርፉ በተቀመጡት የሰራተኞችና የሙተኞች የስነ-ምግባር ዲስፒሊን መመሪያ እንዲሁም በተቋሙ አስተዳደራዊ ደንቦች ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል፡፡

ለምሳሌ አንድ የህክምና ባለሙያ ወይም መሃንዲስ በሙያ ተግባራቸው የጥቅም ግጭት ውስጥ መግባታቸው ከተረጋገጠ ለተወሰነ ጊዜ ከሙያቸው መታገድ እስከ የሙያ ፍቃደ መሰረዝ የሚደርስ ውሳኔ ሊጣልባቸው ይችላል፡፡

የመንግስት ሰራተኛም ሆነ ማንኛውም ዜጋ በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ መስሪያ ቤት እና ድርጅቶች … ወዘተ ከፍተኛ የሆኑ የጥቅም ግጭት ተግባራት ከፈፀሙ በሙስና ወንጀል ህጎች

ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ለዚህም ከተፈፀመው ድርጊት ጋር ቀጥታ ተያያዥ በሆኑ የወንጀል ድንጋጌዎች ለፍርድ ውሳኔ ሊቀርብ ይችላል፡፡

የጥቅም ግጭት ድርጊቶችን ለፍትህ ለማቅረብ የሚያስችሉ በርጀካታ የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎችን እናገኛለን፡፡ የሚከተሉት ድንጋጌዎች በምሳሌነት የሚጣቀሱ ናቸው፡፡

- በስልጣን አለግባብ መገልገል (አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 1-4)
- የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 1-3)
- የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 1-9)
- በስልጣን ወይም በሃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 1-3)
- ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት (19 ንዑስ አንቀፅ 1-3)
- ያለ አግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ (አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 1-3)
- የሥራ ሚስጢር መግለፅ (አንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 1-3)
- የመንግስትዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሀሰት መለወጥ ወይም በሐሰት ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23 ንዑስ አንቀፅ 1-4)
- መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ (አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 1-4)
- ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (25 ንዑስ አንቀፅ 1-6)
- ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት (26 ንዑስ አንቀፅ 1-2)

**የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች**

አንድ የመንግስት ዩኒቨርሲቲ ባወጣው የእቃዎች ግዥ ጨረታ ላይ አንድ ከውጭ ሃገር ኩባንያ ጋር በሽርክና የሚሰራ ድርጅት እጅግ ከፍተኛ በሚባል ዋጋ (በ400 ሚሊን ብር) ጨረታውን አሸነፈ፡፡ ሆኖም የግዢው ሂደትና መካሄድ የነበረበት የስምምነት ፊርማው እጅግ ዘገየ፡፡ በዚህ ሂደት ኩባንያው የአደጉ ሀገራትን የቴክኖሎጂ ደረጃ በአካል እንዲጎበኙ ድርጅቱ የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዝዳንት ጨምሮ ለግዥ ኮሚቴ ሰብሳቢና ለተወሰኑ የማነጅመንት አባላት የውጪ ሃገር ጉዞ አመቻቸ፡፡ እነዚህ የዩኒቨርሲቲ አባላትም በቀረበላቸው ግብዣ መሰረት የ5 ቀናት ጉብኝት ወደ ተባለው ሃገር ተጓዙ፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግዥው ተጠናቀቀ፡፡

- ከላይ በቀረበዉ ኬዝ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩ፡፡

1. ግብዣውን መቀበላቸው አግባብነት አለው ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምን?

2. የዚህ ዓይነት ተግባራት ያላቸውን አወንታዊና አሉታዊ ውጤቶች አብራሩ?
3. በተቋም ደረጃ የዚህ አይነት ተግባራትን ለማስተዳደርና ለመከላከል ምን ዓይነት ስራዎች ሊሰሩ ይገባል ትላላችሁ?መሰል ተሞክሮዎችና አጋጣሚዎች ካላችሁ አብራሩ?
4. በሃገራችን ተቋማት ከላይ የቀረበው አይነት አጋጣሚ መከላከል የሚስችሉ ስርዓቶች፣ አሰራሮችና ህጎች አሉ? በዝርዝር አስቀምጡ?

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

ሀገራት በዋናነት የጥቅም ግጭትን ለመከላከል ከሰዎች የሞራል ማንነትና ስብዕና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ያነሳሉ፡፡ የተለያዩ ህጎችን፣ መርሆችንና አስፈላጊ ስልቶችን በመቀየስ በሰዎች አዕምሮ እንዲሰርፁ በማድረግ እንዲሁም ከተፈፀሙ በኋላ በህጎችና በአዋጆች ከመዋጋት ይልቅ አሰራሮች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት እንዳለበት ያምናሉ፡፡ በዚህም የመከላከል ተግባራዊነትን ለማረጋገጥ የስነ-ምግባር ደንቦችን፣ መመሪያዎችን እና አስፈላጊ የሆኑ ተቋማዊ አሰራሮችን በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር የተለያዩ የክልከላ ህጎችን በማዉጣት ተላልፈዉ የተገኙ የመንግስት ባለስልጣናትን እና ሰራተኞችን በተቀመጠዉ ህግ መሰረት ተገቢዉን ቅጣት እንዲያገኙ በማድረግ የጥቅም ግጭትን በሰፊው ይከላከላሉ፡፡ በመሆኑም በዲሞክራሲ ያደጉ እንዲሁም በኢኮኖሚ የበለፀጉ የውጭ ሃገራት የጥቅም ግጭትን ለመከላከል ያላቸው ልምድና ተሞክሮ፣ በሃገራችን የጥቅም ግጭትን ለመከላከልና ለማስተዳደር እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎችንና በተግባር ላይ እየዋሉ ያሉ ነባራዊ ሁኔታዎችን እንዲሁም በሃገራችን ያለው ገፅታ ምን እንደሚመስል በዚህ ምዕራፍ ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥቅም ግጭት የማስተዳደርና መከላከል የተለያዩ አካላት ሚና

### መግቢያ

የተለያዩ አካላት በተሰጣቸው የመወሰን ስልጣንና ሃላፊነት እንዲሁም በግል ጥቅማቸው መካከል ሊፈጠር የሚችልን የጥቅም ግጭትን የማስተዳደርና የመከላከል ስራዎችን አጠናክሮ መስራት አስፈላጊና ተገቢ ጉዳይ ሆኖ ይስተዋላል፡፡ በዚህ ረገድ ከፍተኛ ኃላፊነት ከተጣለበት መንግስት ስርዓት እና የመንግስት ተቋማት የጎላ ድርሻ ቢኖራቸውም በየደረጃው የሚገኙ የተለያዩ አካላት ሚና እና አስተዋፅዖ እጅግ የጎላ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በዚህ ክፍል ውስጥ የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ብልሹ የአሰራርና የመወሰን ችግሮችን በመከላከል ረገድ የላቀ ድርሻ ያላቸውን አካላት እና እነዚህ አካላት ሊወጡት ስለሚገባ ሚና በዚህ ክፍል ውስጥ ለመዳሰስ ይሞከራል፡፡

ስለዚህ መንግስት፣ የተቋማት አመራርና ሰራተኞች፣ የሲቪክ ማህበራትና ሚዲያ፣ እንዲሁም ህብረተሰቡ የጥቅም ግጭት በመከላከል የላቀ ሚና እንዳላቸው የክፍል አራት አንኳር ጉዳዮች ናቸው፡፡

### የምዕራት አራት ዝርዝር ዓላማ

ከዚህ ትምህርት በኋላ ሰልጣኞች:-

- የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚመለከታቸውን አካላት ሚና ለይተው ይዘረዝራሉ፡፡
- የጥቅም ግጭትን ለመከላከልና ለማስተዳደር የተቋማት አመራርና ሰራተኞች ሊተገብሯቸው የሚገቡ ሚናዎችን በተቋማቸው ይተገብራሉ፡፡
- የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የወጡ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎችን በተቋማቸው ተግብረው ያስተዋውቃሉ፡፡
- በሃገር ደረጃ የጥቅም ግጭትን በመከላከል እና በማስተዳደር ኃላፊነት ያለበት እና ተጠያቂ አካል ማን እንደሆነ በግልፅ ያሰረዳሉ፣

### የማሠልጠኛ ዘዴዎች

- ገለጻ፤
- የጥንድና የቡድን ውይይት፣
- አስረጅ ጥናት፣
- ልምድ ልውውጥ

**የመርጃ መሣሪያዎች**

- ፓወር ፖይንት፤
- ማርከር፤
- ፍሊፒቻርት፣
- ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች (ስፖት፣ ድራማ)

**የሚፈጀዉ ጊዜ** 4፡00 ሰዓት

## 4.1 የጥቅም ግጭት የማስተዳደርና የመከላከል ኃላፊነት እና የተለያዩ አካላት ሚና

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

1. የጥቅም ግጭትን ለመከላከል ኃላፊነት አለባቸው የምትሏቸውን አካላት ዘርዝሩ?
2. ተዘረዘሩት አካላት ሊወጡት የሚገባቸው ሚና ዘርዝሩ?

የጥቅም ግጭት እንደማንኛውም የሙስና ወንጀሎች ለመከላከል የብዙ አካላት ተሳትፎ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ከማንኛወም ዜጋ እስከ ከፍተኛ የመንግስት አካላት በትብብርና በቅንጅት መስራትና በተናጠልም እነዚህ አካላት የሚያደርጉት አስተዋፅኦ ችግሩን በመከላከል ረገድ መሰረታዊ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡ በዚህ ረገድ በዚህ ክፍል የጥቅም ግጭትን በመከላከል የላቀ ሚና ያላቸው አካላት እና እነዚህም አካላት ሊወጧቸው የሚገቡ ተግባራት ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡

### 4.1.1 ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው አካላት

**1. የመንግስት ሚና**

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- መንግስት የጥቅም ግጭትን በማስተዳደርና በመከላከል ደረጃ ምን ዓይነት ሚና ሊጫወት ይገባል ትላላችሁ? ዘርዝሩ?

በአሁኑ ወቅት ስለመንግስት አስተዳደርር ስርዓት ያለው ግንዛቤና እና እሳቤ መንግስት ከማንኛውም አካል በላቀ የዜጎችን እና የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ መብትና ጥቅም የማስከበር እና የማስጠበቅ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በዚህ ረገድ የዜጎችና የማህበረሰብን ጥቅምና መብት የሚጎዱ ድርጊቶች ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን እንዲሁም የጥቅም ግጭት ድርጊቶችን የሚከላከሉ ተጨባጭ ስራዎችን የመስራት ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ ረገድ መንግስት የጥቅም ግጭትን ለመከላከልና ለማስተዳደር መስራት ካለበት ተግባራቶች መካከል የሚከተሉት በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

- የጥቅም ግጭት የሚከላከሉና የሚያስገነዝቡ ወቅታዊ ህግጋትን ማውጣት፣
- የጥቅም ግጭትን በኃላፊነት የሚከታተልና የተቋማትን ብቃት የሚያሳድግ ራሱን የቻለ ተጠያቂ የሚሆን ተቋም ማቋቋም፣
- ተገቢውን የድጋፍና ክትትል ስራ መስራት፣
- ጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚያስችሉ አመላካች ኃሳቦች እንደተካተቱ መረዳትና ጉዳዩ ትኩረት እንዲያገኝ ማድረግ፣
- በችግሩ ዙሪያ የፖሊቲካ ቁርጠኝነትን የሚመለከቱ የተጠያቂነት አሰራርን ማጎልበት፣
- በሚስተዋሉ ጥቅም ግጭቶች ዙሪያ ላይ ህ/ሰቡን፣ ሙያተኛውን፣ በአጠቃላይ ዜጎች ግንዛቤያቸውን የማሳደግ ስራዎችን መስራት፣ የነቃ ተሳትፎ እንዲኖረው እምነታቸውን ማጎልበት፣
- አመራሮችና ሃላፊዎች ራሳቸውን ከጥቅም ግጭት በማግለል ለሌላው ማህበረሰብ አርዕያና ሞዴል መሆን የሚችሉበትን የባህሪ ግንባታ ስራዎችን መስራት፣

## 2. የፀረ-ሙስና ተቋማት

### የማነቃቂያ ጥያቄዎች

1. የፀረ-ሙስና እና ሌሎች መሰል ተቋማት የጥቅም ግጭትን በማስተዳደርና በመከላከል ምን ዓይነት ሚና ሊጫወቱ ይገባል ትላላችሁ? ዘርዝሩ?

የጥቅም ግጭትን በመከላከልና በማስተዳደር ከፍተኛ የመንግስት አካል ወይም ተቋም ከሆኑት ጉዳዮች መካከል የፌደራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አንዱና ቀዳሚ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ኮሚሽኑ የተለያዩ ኃላፊነቶችን ይወጣል፣ ለአብነት ያህል የሚከተሉት ጉዳዮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

- በጥቅም ግጭት ዙሪ ህጎችን ፖሊሲዎችን፣ ደንቦችን ማውጣት፣
- እንደየስራ ኃላፊነትና የሙያ ዘርፍ የስነ-ምግባር ደንብ መቅረፅና መተግባር፣
- ተቋማት የጥቅም ግጭት መመሪያ፣ ደንብና ስርዓትን የሚያግዙ አደረጃጀት እንዲፈጥሩ ማገዝ፣ መከታተልና መደገፍ፣
- መድረኮችን፣ ሚዲያዎችን ወዘተ በመጠቀም መጠነ ሰፊና ሙያ ተኮር የግንዛቤና የአቅም ግንባታ ስራዎችን መስራት፣
- የጥቅም ግጭት ፈፅመው የተገኙ አካላትን ወደ ህግ የሚቀርቡበትን ስርዓትና አሰራር መዘርጋት፣

## 3. የተቋማት አመራርና ሰራተኛ ሚና

1. የተቋማት አመራርና ሰራተኞች የጥቅም ግጭትን በማስተዳደርና በመከላከል ምን ዓይነት ሚና ሊጫወት ይገባል ትላላችሁ? ዘርዝሩ?

የመንግስታዊ ተቋማት ዋና እና ቀዳሚ ወኪሎች የተቋማት አመራሮች መሆናቸው ይታወቃል፡፡ እነዚህ አመራሮች በመንግስት የሚቀረፁ ህጎችና ደንቦችን በይበልጥ ከጥቅም ግጭት ጋር በተያያዙ የሚቀየሱና የሚነደፉ ስልቶችን ተግባራዊ እንዲሆኑ የማድረግ ምሳሌያዊ ስራዎችን በንቃት ሊሰሩ ይገባል፡፡ በተመሳሳይ ከአመራሩ በተጨማሪ እያንዳንዱ የተቋም ሰራተኛም የጥቅም ግጭትን በመከላከል ረገድ ያላቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡

የጥቅም ግጭት ተግባራት የሚፈፅሙት የተቋማት አመራርና ሰራተኞች የመንግስት ስራዎችን እና አገልግሎቶችን የሚወጡ አካላት በመሆናቸው በነዚህ አካላት አማካኝነት ነው፡፡ በዚህ የተነሳ እነዚህ አካላት በማንኛውም የኃላፊነትና የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት የጥቅም ግጭት ተግባራትን በመከላከል የላቀ ሚና እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህ አካላት ከሚሰሯቸው ተግባራት መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

- የጥቅም ግጭትን በመከላከል፣ ራሳቸውን ከጥቅም ግጭት ተግባራት ነጻ በማድረግ የሰብአዊነት ባህሪን መላበስ፣
- የግልፅነትና ተጠያቂነትን መርህ በማስፈን የመንግስት እና የግል ኃላፊነት በላቀ ስብዕና መወጣት፣
- ተቋማት የራሳቸውን የጥቅም ግጭት የሚከላከሉበትን ህግና መመሪያ በማውጣት በሚገባ ተግባር ላይ የሚውሉበትን መንገድ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የማይተካ ሚናቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የመንግስት ባለስልጣናትና ሠራተኞች በተሰጣቸው የመወሰን ስልጣንና በግል ጥቅማቸው መካከል ሊፈጠር የሚችልን የጥቅም ግጭትን በመለየት የስነምግባር መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣ ማፅደቅና ተግባራዊ ማድረግ፣
- ከጥቅም ግጭት መከላከል ጋር በተያያዘ ለተቋሙ አመራርና ሰራተኞች፣ ለባለድርሻ አካላት፣ ለደንበኞችና ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርትና ስልጠና መስጠት፤
- ለጥቅም ግጭት የሚዳርጉ ክፍተቶችን፣ ህጎችን፣ አሰራሮችን በጥናት በመለየት የማስተካከያ እርምጃ መውሰድና እንዲስተካከሉ ማድረግ፣

- በጥቅም ግጭት ዙሪያ የተለያዩ ሀገራትን መልካም ተሞክሮ በማጥናትና ልምድ በመውሰድ እንዲተገበር ማድረግ፤
- የተቋሙ አመራርና ሠራተኞች የስነ ምግባር መመሪያዎችና ደንቦች እንዲተገበሩ የተለያዩ ድጋፎችና ክትትሎች ማድረግ፤
- ከጥቅም ግጭት ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን ተቀብሎ ተገቢውን ህጋዊ እልባት መስጠትና የእርምት እርምጃዎችን መውሰድ፣

በሌላ መልኩ የጥቅም ግጭትን በመከላከልና በማስተዳደር ተቋማዊ ነባራዊ ሁኔታን በዳሰሰ መልኩ የሚተገበሩና የሚሰሩ ስራዎች እጅግ መሰረታዊ ናቸው፡፡ ከነዚህ በተቋም ደረጃ ሊሰሩ ሚገባቸው መከላከያ ስልቶች መካከል የሚከተሉትን ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህ ስልቶች በተወሰነ ደረጃ በሃገራችንም የሙስና እና ጥቅም ግጭትን መከላከል በሚያስችሉ ህጎች ውስጥ ሰፍረው እናገኛለን፡፡

### 1. የጥቅም ግጭት ስጋቶችን መዝግቦ መያዝ /register

ለጥቅም ግጭቶች ይዳርጋሉ ተብለዉ የሚታሰቡትን ጉዳዮች በሚመለከተዉ አካል በዝርዝር ተመዝግቦ እንዲያዝ ማድረግ፤ይህም የጥቅም ግጭት የስጋት አካባቢዎችን መዝግቦ መያዝ አፋጣኝ የመከላከያና የማስተዳደሪያ መንገዶችን ለመቀየስ መነሻ ሃሳብ መውሰጃ ይሆናል፡፡

### 2. ከተሳትፎ ማገድ/restrict/

የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ለአንዳንድ ጉዳዮችና ስራዎች ያላቸው ግላዊ የጥቅም ግጭት ይፈጥራል ተብሎ ከታሰበ የስራ ኃላፊውን ወይም ሰራተኛውን ከማንኛውም ዓይነት የኮሚቴና የሙያ ውሳኔ ከመስጠት እንዳይሳተፍ ማድረግ፡፡ በሌላም በኩል ብልሹ የንግድ ስርዓትና የስነ-ምግባር እሴትን የማያከብር ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ ድርጅትን ከማንኛውም ጨረታ ውድድር እቀባ እስከማድረግ የሚደርስ እርምጃዎችን ማስተላለፍ ጭምርን ያካትታል፡፡

### 3. በገለልተኛ አካላት ማጣራት/recruit/

የጥቅም ግጭቱ ተከሰተ ከተባለ እና ከበቂ በላይ ጥርጣሬ ከተፈጠረ ጉዳዩን በገለልተኛ ኮሚቴ እንዲታይ ማድረግ ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ አሰራር የጥቅም ገጭት መከላከልና ማስተዳደር ስራው ነፃ እና ውጤታማ እንዲሆን፣ እንዲሁም ከግል ፍላጎት ይልቅ የሕዝብ ጥቅም ማስቀደምን መሰረት ያደረገ ውሳኔ ለመወሰን ያስችላል፡፡

4. **እራስን ማግለል** /removal or recuse/

ለጥቅም ግጭት ይዳርጋሉ ተብለዉ የተመዘገቡት እና ሌሎችም በዉሳኔ አሰጣጥ ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ ተብለዉ የሚታሰቡ ጉዳዮችን ላለማየትና ዉሳኔ ላለመስጠት በፍቃደኝነት እራስን ከዉሳኔ ማግለል፡፡

5. **ማስተላለፍ ወይም መሸጥ** /relinquishe or divestiture/

ለግጭቱ መነሻ የሆነውን የግል ኢንተርኘራይዝ፣ ካምፖኒ ወይም የንግድ ድርጅት ድርሻውን ማስተላለፍ ወይም ማቋረጥ፣ ወይም በግል የያዘውን ኢንቨስትመንትና የግል ድርጅት በወኪል ማሰራትና ካፒታልና ትርፉን በማያዝበት የባንክ ሂሳብ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

6. **ከስራ መልቀቅ/መሰናበት** /resign/

ከመንግስት ስራ በተደራቢነት ከሚሰራበት የግል መ/ቤት፣ በቦርድ አባልነት፣ በዳይሬክተርነት፣ በአማካሪነት ወዘተ የያዘውን ኃላፊነት መልቀቅ፣

7. **ሀብት ማሳወቅ**/disclosure/

በራሱ፣ በልጆቹ፣ በባለቤቱ እና በቅርብ ዘመዶቹን በሚያስተዳድራቸዉ የስጋ ዘመድና የጋብቻ ግንኙነት ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ ሀብት እና በየወቅቱ የሚገኙ ገቢዎችን ማስመዝገብ የሚገባ ሲሆን፣ ይህም እያንዳንዱ የመንግስት ኃላፊ አና የመንግስት ሠራተኛ የራሱ የሆነው የግለ ፍላጎትና የህዝብ ፍላጎት በየራሳቸው መንገድ የሚመሩበትን ሁኔታ ከማመቻቸቱም በላይ አሰራሩ ግልፅ ሁኔታን ሊፈጥር ስለሚችል የግልና የሕዝብ ፍላጎት ሳይቀላቀል እንዲሁም የጥቅም ግጭት ሳይፈጥር ስራዎች በተቀመጠላቸው ስታንዳርድና ህግ መሰረት እንዲሄዱ የሚያስችል ይሆናል፡፡

8. **ስጦታ እና መስተንግዶ**

ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኑ የመወሰን ስልጣኑን የሚፈታተን፣ ውሳኔውን የሚያዛባና የጥቅም ግጭትን የሚፈጥር ስጦታን፣ መስተንግዶን ወይም ሌላ ጥቅምን አለመቀበል፣ወይም የተቀበለዉን ማሳወቅ አለበት፡፡

### 4.1.2 ሌሎች ባለድርሻ አካላት

#### 1. የሲቪል ማህበራትና ሚዲያ ሚና

***የማነቃቂያ ጥያቄዎች***

- የሲቪል ማህበራትና ሚዲያ የጥቅም ግጭትን በማስተዳደርና በመከላከል ምን ዓይነት ሚና ሊጫወት ይገባል ትላላችሁ? ዘርዝሩ፡፡

የሲቪል ማኅበራት የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩና የኅብረተሰብ ተሳትፎ በማጎልበት ረገድ የጎላ ሚና አላቸው፡፡ መንግስት ህግና ደንብን በመቅረፅ በመተግበር የመንግስት አስተዳደር ስርዓት ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዳ መሆኑን የመከታተል፣ የማሳወቅ፣ ህ/ሰቡን የማስተማርና የማንቃት ስራዎችን የመስራት አቅምና ኃላፊነት አለበት፡፡ በዚህ ረገድ የጥቅም ግጭት አንዱ በመንግስት መዋቅር ስልጣንና ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ የሚስተዋል እኩይ ተግባር በመሆኑ፣ እነዚህ አካላት፡-

- የጥቅም ግጭት በማጋለጥና ችግሩ እንዲስተካከል በማድረግ ረገድ የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡
- መንግስት ብልሹ አሰራር መከላከል ስርዓት የሚያጠናክሩ ስራዎችን እንዲሰራ ተገቢውን ግፊትና ድጋፍ ማድረግ፣
- ህብረተሰቡን በተለያዩ መንገዶች ስለ ጥቅም ግጭት እንዲሁም አጠቃላይ ስለሙስናና ብልሹ አሰራር የሚቀረፍበትን ሁኔታ ማስተማርና ማሳወቅ፣
- በመንግስት አስተዳደር ስርዓት ውስጥ የሚፈፀሙ ብልሹ ተግባራትን የጥቅም ግጭትን ጨምሮ እንዲከላከል፣ እንዲቃወምና እንዲጠቁም የማድረግ አቅምና ግንዛቤ ስራዎችን መስራት፣
- መንግስትን ለችግሩ ትኩረት እንዲሰጥ ተገቢውን ሙያዊና ቁሳዊ ድጋፍ ማድረግ፣
- ሃላፊዎችና የመወሰን ስልጣን ያላቸው ግለሰቦችና ባለሙያዎች የጥቅም ግጭትን በማሰወገድ ሃላፊነትታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ማስተማረርና ማንቃት፣
- በመንግስትና በህዝቡ መካከል መረጃዎችንና ተሞክሮዎችን የማጋራት ስራ መስራት፣
- ሚዲያ የጥቅም ግጭት የሚመለከቱ እውነታዎችን፣ ጥቆማዎችን፣ ፍንጮችን፣ ቅሬታዎችን በማስረጃ እያስደገፈ ለሕዝብ ይፋ በማድረግ፣ በማሳሰብ የተቋማት አመራርና ሰራተኞች የጥቅም ግጭት ችግር ውስጥ እንዳይገቡ የማስተማርና የማስጠንቀቅ ስራዎችን መስራት ይኖርበታል፡፡

## 2. የሙያ ማህበራት

### የማነቃቂያ ጥያቄዎች

1. የሙያ ማህበራት የጥቅም ግጭትን በማስተዳደርና በመከላከል ምን ዓይነት ሚና ሊጫወቱ ይገባል ትላላችሁ? ዘርዝሩ?

በሃገራችንም ሆነ በተለያዩ ሃገራት ከፍተኛና የላቀ ሙያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች የሚሰጡ እጅግ ክቡር የሆኑ ሙያዎችን እናገኛለን፡፡ ለአብነት ያህል የህክምና ባለሙዎች፣ የህግ ነክ ሙያዎች፣ ጋዜጠኞች፣ የሂሳብ መዝገብ ሙያዎች፣ ምህንድስና፣ መምህራን ወዘተ..ለጥቅም ግጭት እጅግ ተጋላጭ ሙያዎች እንደሆኑ ማስረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በዚህ ምክንያት የእነዚህና መሰል የሙያ ዘርፎች ማህበራትና የአካዳሚክ ትምህርትና የእውቀት ዘርፎች በጥቂቱ የሚጠቀሱ ሲሆኑ እነዚህ ሙያተኞች የሙያ ስነ-ምግባራቸውን አክብረው ህዝብን እንዲያገለግሉ የማድረግ ስራዎችን ሳይታክቱ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሁሉም ዓይነት የሙያ ስነ-ምግባሮች በትምህርትም ደረጃ ሆነ በስራ ኃላፊነት ላይ ሲሰማሩ የጥቅም ግጭት ተግባራት እንዲርቁ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ በዚህና በሌሎች ምክንያቶች የሙያ ማህበራት የጥቅም ግጭቶችን በመከላከልና በማስተዳደር ረገድ ሊከውኗቸው ከሚችሉ ስራዎች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

- የሙያ ስነምግባር መሰረታዊ ዓላማ የሆነውን መርህ ማለትም፣ ባለሙያዎች በሙያቸውና ስብዓናቸው የላቁ እንዲሆኑ በማስቻል የህዝብ ጥቅምና መብት ከሚጎዱ ተግባራት እንዲርቁ የማስቻል ስራዎች ላይ አጠንክሮ መስራት፣
- ለሙያ ማህበሩ አባላት በየዘርፉ የስልጠናና አቅም ግንባታ ስራዎችን መስራት፣
- የሙያ ማህበራትን ጥምረት ማጠናከር እና መልካም ተሞክሮዎችን መለዋወጥ፣
- ሙያተኞች ለስነ-ምግባር መመሪያቸው ተገዢ የሚሆኑበትን የተጠያቂነት አሰራር ማጠናከር፣
- ከሌሎች የጥቅም ግጭትና ሙስና ከሚከላከሉ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የትብብርና የቅንጅት ስራዎችን ማጠናከር፡፡

## 3. የህበረተሰብ ሚና

### የማነቃቂያ ጥያቄዎች

➢ ህብረተሰብ የጥቅም ግጭትን በማስተዳደርና በመከላከል ምን ዓይነት ሚና ሊጫወት ይገባል ትላላችሁ? ዘርዝሩ?

በመንግስት ተቋማት የሚፈፀሙና የሚስተዋሉ የጥቅም ግጭትን ጨምሮ ማንኛውንም ዓይነት ብልሹ አሰራሮች የህብረተሰቡ ተሳትፎ ከሌለበት የሚፈለገውን ውጤት ማግኘት አዳጋች ይሆናል፡፡ የጥቅም ግጭትና ማንኛውም ዓይነት በመንግስት ስልጣንና ኃላፊነት አላግባብ በመገልገል የሚገኝ የወንጀል ፍሬ ውጤት ከህዝብ ዓይን የሚሰወር አይሆንም፡፡

በዚህ ረገድ ህብረተሰቡ የጥቅም ግጭት ጉዳዮችን በመከላከል ረገድ ሊጫወት ከሚገባቸው ሚናዎች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

- ስለጥቅም ግጭት የሚተላለፉ አስተምህሮዎችንና ግንዛቤን ማሳደግ፣
- የጥቅም ግጭት ድርጊቶችን ማጋለጥ፣
- ችግሩ ሲያጋጥማቸውና ሲጠረጥሩ ጉዳዩን በፍጥነት ለሚመለከታቸው አካላት ጥቆማ በመስጠት ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

### የቡድን ውይይት ጥያቄ

አብዛኛውን ጊዜ በመንግስት ተቋማት ውስጥ ለሚስተዋሉ ብልሹ አሰራርና የጥቅም ግጭት ለመንሰራፋት መንግስት ራሱ የፈቀደው ነው የሚል አመለካከት ይንፀባረቃል፡፡ አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት ደግሞ የተቋማትን የስራ ኃላፊዎችና ባለሙዎች ለሙስና እና ለጥቅም ግጭት የሚጋብዘው ራሱ ህዝቡ ነው የሚል ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ ችግር ካለም በሂደት የሚስተካከል የሚሆን ነው የሚል ምላሻ ይሰጣሉ፡፡ በእነዚህ የሀሳብ ውዝግብ የዜጎች መብትና ጥቅም ላይ የሚደርሰው ጉዳት እየተጠናከረ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡

በዚህ ሁኔታ የትኛው አሰተሳሰብ ትክክል ነው ትላላችሁ? ለምን? የዚህ ዓይነት ግንዘዛቤ ካላችሁ በምሳሌ አስረዱ፡፡

➢ እርሶ እንደ አንድ ከፍተኛ ባለሙያ የመፍትሄ ሀሳቦች እንድታቀርቡ ቢጋበዙ ሁኔታውን ለመቀየር ምን ዓይነት መሰረታዊ ምክር ይለግሳሉ? የዚህ ዓይነት ሁኔታዎችን እንዴት ማስተካከል ይቻላል? እርምጃዎች/ ተግባራትን አብራሩ፡፡

**የምእራፉ ማጠቃለያ ጥያቄ**

በአሁኑ ወቅት ከሁሉም አካላት በላይ ብልሹ ተግባራትን መከላከል፣ የጥቅም ግጭት መከላከልን ጨምሮ በሚሰሩ ስራዎች የሚዲያ አካላት ሚና የጎላና በርካታ ቁጥር ያላቸው አካላትን እናገኛለን፡፡ ያም ሆነ ይህ የሚዲያ አካላት በበዙበት ሃገር ከፍተኛ የሞራልና የስነምግባር መዝቀጥ ይስተዋላል የሚል ቅሬታዎች ተበራክተው እናገኛለን፡፡

1. ይህ አስተሳሰብ/ ሚዲያ በተስፋፋበት ሁኔታ ለምን ከፍተኛ የሙያና የስራ ስነምግባር ድክመት ይታያል ተብሎ ግምት ተወሰደ? ይህ ሁኔታ ምንን ይገልፃል?
2. ከሁሉም የጥቅም ግጭት መከላከል ኃላፊነት ካለባቸው አካለት መካከል ሚዲያ እና ሲቪክ ማህበራት የላቀ ደርሻ እንዳላቸው ይነገራል፡፡ በሃገራችን ሁኔታ የእነዚህ አካላት አስተዋፅዖ  ምን ገፅታና መልክ አለው፡፡ በምሳሌ አብራሩ፡፡

## የሞጁሉ ማጠቃለያ

ይህ የጥቅም ግጭት ሞጁል ትኩረት ከማግኘት ጀምሮ፣ ጽንሰ ሃሳቡን ትርጓሜ፣ ከሙስናና ብልሹ ተግባራት ጋር ስላለው ልዩነትና አንድነት፣ መገለጫዎቹ፣ በአለም አቀፍና በሃገራችን የተቀየሱ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ስላሉ የመከላከያ ስልቶች፣ የጥቅም ግጭት በዜጎች፣ በህብረተሰብ መብትና ጥቅም ላይ ስለሚደርሰው ጉዳት  የጥቅም ግጭትን በመከላከል ረገድ የላቀ ሚና ያላቸውን አካላት እንዲሁም እነዚህ አካላት ሊያከናውኗቸው ስለሚገባ ተግባራት በስፋት ያብራራል፡፡  የጥቅም ግጭት መከላከል ተገቢ የሆነው ከጊዜ ወደ ጊዜ በመንግስት አሰራርና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ መጠነ ሰፊና ዘርፈ ብዙ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አጠቃላይ በዜጎች መብትና ጥቅም ላይ የሚደርሰው ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት የመንግስት አስተዳደር ስርዓት ግልፅነት ያለውና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን ብሎም የሃገር እድገትና ሰላም እንዲረጋገጥ በመንግስት አሰራርና አስተዳደር ስርዓት ውስጥ ሙስና ብልሹ አሰራሮች መከላከል የማንኛውም መንግስታዊ አካልና ተቋም ተቀዳሚ ኃላፊነት ነው፡፡ ለዚህም መንግስትና እያንዳንዱ የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት የስራ ኃላፊነታቸውና ባለሙያዎች ኃላፊነት እየሰፋና እያደገ መሄዱን መመልከት ይቻላል፡፡ በዚህም የተነሳ መንግስትና ይበልጥ የጸረ-ሙስና ተቋማት ምክንያት የጥቅም ግጭትን በመከላከልና በማስተዳደር ትኩረት አድርገው ሊሰሩ እንደሚገባ ነባራዊ ሁኔታዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከሚሰሯቸው ተግባራት መካከል የጥቅም ግጭትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ህጎች ከማዘጋጀትና ከማፀደቅ ጀምሮ አፈፃፀማቸውን መከታተል፣ በሃሳቡ ዙሪያ መጠነ ሰፊ የግንዛቤ ማበልፀጊያ ስራዎችን መስራት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ሞጁሉ የጥቅም ግጭት ባህሪያትን ለጥቅም ግጭት የተጋለጡ የስራ ክፍሎችን፣ ችግሩን እንዴት መከላከል እንደሚቻል፣ መከላከያ ስልቶችን፣ ችግሩን በመከላከል ቀዳሚ ኃላፊነት ያለባቸው ተቋማት እና  ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በመለየት፤ ያላቸውን ሚና እና ሊዘረጉት ስለሚገባ አሰራሮች አቅጣጫ ይሰጣል፡፡

## ዋቢ ማጣቀሻዎች (References)


Managing Conflict of Interest OECD 2015

በተባበሩት መንግሰስታት ፀረ ሙስና ኮንቬንሽን UNCAC proc 544/2007

አዋጅ ቁጥር 668/2002

የ1987 ዓ.ም የኢፌዴሪ ህገ መንግስት

የሙስና እና የስነምግባር ማሰልጠኛ ሞጁሎች (ፌስፀሙኮ 2008)

የሙስና ወንጀል ምርመራ ክስ የስልጠና ሰነድ (2014)

የተሻሻለው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013

የተሻሻለው የሙስና ወንጀል ህግ አዋጅ ቁጥር 881/2007

የአፍሪካ ሕብረት የፀረ-ሙስና መከላከያና መዋጊያ ኮንቬንሽን AUCAC 545/2007

የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደርን አስመልክቶ የተዘጋጀ የስልጠና ሰነድ (አአከስፀሙኮ 2016)